የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የ2008 በጀት ዓመት የተደገፈ በጀት

ጥራዝ I በጀት ማጠቃለያ

ግንቦት **26/2007**

ማውጫ

ገጽ

1 መግቢያ 1

2. የአጠቃላይ ኢኮኖሚ አፈጻጸም 3

2.1 የኢኮኖሚ ዕድገት 3

2.2 የዋጋ እንቅስቃሴ 4

2.3 የወጪና ገቢ ንግድ አፈጻጸም 6

2.4 የገንዘብ እንቅስቃሴ አፈጻጸም...8

2.5 የፊሲካል ፖሊሲና የመንግስት ፋይናንስ አፈጻጸም.....................................9

2.5.1 ሀገራዊ ጠቅላላ የመንግሥት ገቢ አፈፃፀም 10

2.5.2 ሀገራዊ የመንግሥት ወጪ አፈፃፀም...13

2.5.3 የበጀት ጉድለት...16

3. የ2007 በጀት ዓመት የአጠቃላይ ኢኮኖሚና ፊሲካል አፈፃጸም ዕይታ 17

3.1 የአጠቃላይ ኢኮኖሚ አፈጻጸም 17

3.2 የፊሲካል ፖሊሲና የፌዴራል መንግስት ፋይናንስ አፈፃፀም..................... 20

3.2.1 የገቢና ዕርዳታ አፈጻጸም...20

3.2.2 የወጪ አፈጻጸም..22

4. የ2008 በጀት ዓመት ገቢ፣ ወጪና የወጪ አሸፋፈን..22

4.1 አጠቃላይ ታሳቢዎች...24

4.1.1 የአጠቃላይ ኢኮኖሚ ታሳቢዎች..24

4.1.2 የፊሲካል ፖሊሲዎች ታሳቢዎች..25

4.2 የፌዴራል መንግስት ገቢ………………………………………………..……26

4.3 የመደበኛ ወጪ 28

4.4 የካፒታል ወጪ 28

4.5 የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የበጀት ድጋፍ 29

4.6 የዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ 30

5. የ2008 ፕሮግራም በጀት አዘገጃጀትና ድጋፍ 31

5.1 የ2008 ፕሮግራም በጀት ዝግጅት ዋና ዋና ታሳቢዎች 31

5.1.1 ጠቅላላ ታሳቢዎች 31

5.1.2 የመደበኛ ወጪ 33

5.1.3 የካፒታል ወጪ 34

5.2 ጠቅላላ በጀት 36

5.2.1 የመደበኛ ወጪ 37

5.2.2 የካፒታል ወጪ 41

5.2.3 የ2008 የፌዴራል ወጪ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው 44

6. የወጪ አሸፋፈን 46

1. መግቢያ

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (GTP) መሪ አጀንዳ የሆነውን ፈጣን፣ መሠረተ ሰፊና ፍትሐዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ የተያዘውን ዕቅድ በስኬት ለመደምደም ከፍተኛ ርብርብ ተደርጓል፡፡ ባሳለፍናቸው አራት የዕቅዱ ትግበራ ዓመታትና በያዝነው በጀት ዓመት በርካታ ታላላቅ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ በዚህም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከ2003-2006 ባሉት የዕቅዱ ትግበራ ዓመታት በአማካይ የ10.1 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት አስመዝግቧል፡፡ ምንም እንኳን በ2003-2006 የተመዘገበው ዕድገት በዕቅዱ ከተያዘው በመጠኑ ዝቅ ያለ ቢሆንም በአጠቃላይ ሲታይ የተመዘገበው ዕድገት በማንኛውም መሥፈርት ከፍተኛ የሚባልና ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ዕድገት ነው፡፡ ዕድገቱም በሁሉም ዘርፎች በህብረተሰቡ፣ በግሉ ዘርፍና በመንግስት በተደረገ ሰፊ ተሳትፎና ርብርብ የተመዘገበ ነው፡፡ በተለይም በመንግስት በኩል፣ ከሀገር ውስጥና ከውጭ የተገኘውን የልማት ፋይናንስ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን ለማስፋፋት በጀት በመመደብና በጀቱም ለታለመለት ዓላማ እንዲውልና ውጤቶች እንዲመዘገቡ በማድረግ ለኢኮኖሚ ዕድገቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ በአጠቃላይ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (GTP) የተያዙ ግቦች አፈጻጸም የተሳካ መሆኑን እስከ አሁን የተደረጉት ግምገማዎች ያሳያሉ፡፡ ሆኖም በወጪ ንግድ እና በማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች የተያዙትን ግቦች በሚጠበቀው ደረጃ ማሳካት አለመቻሉን ከተረደገው ግምገማ መረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አምስት ዓመታት እነዚህ የማኑፋክቸሪንግ እና የኤክስፖርት ዘርፎች ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች ይሆናሉ፡፡ ሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የዘላቂ ልማት ግቦች (Sustainable Development Goals (SDGs)) መሠረት የሚያደርግ ሲሆን ግቦቹም በዋናነት በማኑፋክቸሪንግና በኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን፣ በዘላቂ መሰረተ ልማትና ኤነርጂ እንደዚሁም በኤክስፖርት መስፋፋት ላይ ትኩረት እንደሚያደርጉ ይጠበቃል፡፡

በመጠናቀቅ ላይ ያለው የ2007 በጀት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ማጠናቀቂያና የቀጣዮቹ አምስት ዓመታት ዕቅድ ዝግጅት የሚደረግበት ነው፡፡ በመሆኑም የ2008 የፌዴራል መንግስት በጀት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን በሚቀጥሉት የአምስት ዓመታት ከሚጠበቁ የትኩረት አቅጣጫዎች ጋር ተጣጥሞና በዝርዝር ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ስለዚህም በየዓመቱ እየተዘጋጀ ሥራ ላይ የሚውለው የመንግስት በጀት የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማቶችን ተግባራዊ

በማድረግ ለዕቅዱ መሳካት ቁልፍ ሚና እየተጫወተ እንደሚገኝ ይታወቃል። በተለይም በጀት ከመንግስት ፖሊሲና ስትራቴጂ ጋር እንዲተሳሰርና በረጅምና መካከለኛ ዕቅድ እንዲመራ የሚያደርግ አሰራር መዘርጋቱ ለውጤቱ መፋጠን የራሱ አስተዋጽኦ አድርጓል። በዚህም መሠረት የ2008-2012 የመካከለኛ ዘመን የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ ለበጀት ዝግጅት መነሻነት እንዲያገለግል የተደረገ ሲሆን፣ በማዕቀፉም ላይ በመመሥረት የ2008 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት ዝርዝር የፕሮግራም በጀት ተዘጋጅቷል።

ይህም የተዘጋጀው በጀት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የሚጠበቁ ዋና ዋና የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ግቦችን ዓላማ ለማሳካት በሚያስችልና አሁን የተገኘውን የልማት ውጤት በአስተማማኝ መሠረት ላይ በመጣል የዕድገቱ ቀጣይነት በሚያረጋግጥ፣ የኢንዱስትሪ ልማትና ኤክስፖርትን በሚያስፋፋ፣ የዘላቂ ልማት ግቦችን (SDGs) ለማሳካትና ሀገሪቱን ወደላቀ የልማት ደረጃ ለማሸጋገር ለሚደረገው ጥረት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በሚኖረው መልክ የተዘጋጀ ነው። ለዚህም የመንግስትን በጀት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ ለማዋል የአስፈጻሚ አካላትን ርብርብ ይጠይቃል። በበጀት ዝግጅቱ በ2008 በጀት ዓመት ሊሰበሰብ የሚችለውን የፌዴራል መንግስት ገቢ በተጨባጭ ለመገመት የተሞከረ ሲሆን፣ በተለይ የአገር ውስጥ ገቢ አሰባሰብ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት መሠረታዊ ግምት የተሰጠው ጉዳይ ነው። የወጪ በጀቱ የተዘጋጀው ተግባራዊ እየተደረገ ባለው የፕሮግራም በጀት ሥርዓት መሠረት ነው። እንዲሁም በጀቱ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚን ለማምጣት የሚደረገውን ጥረት በሚደግፍ መልኩ የተዘጋጀ ነው።

በዚህ የበጀት ጥራዝ ውስጥ በቅድሚያ በዕድገትና ትራንስፎርሜን ዕቅዱ የመጀመሪያ አራት የትግበራ ዓመታት የአጠቃላይ የኢኮኖሚና የመንግስት ፋይናንስ አፈፃፀም ዳሰሳ በአጭሩ ቀርቧል። በቀጣይም የያዝነው የ2007 በጀት ዓመት የመጀመሪያ የዘጠኝ ወራት የኢኮኖሚና ፊሲካል አፈጻጸም ዕይታ (Outlook) በአጭሩ ቀርቧል። እንዲሁም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ለ2008 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት የአገር ውስጥና የውጭ ፋይናንስ ዕቅድ ዝግጅት የተወሰዱ ዋና ዋና ታሳቢዎችና ዝርዝር የገቢ ዕቅድ በሰነዱ በመጨረሻው ክፍል ከትንታኔ ጋር ቀርቧል።

2. የአጠቃላይ ኢኮኖሚ አፈፃፀም

2.1 የኢኮኖሚ ዕድገት

ከ2003 እስከ 2006 በነበሩት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ዓመታት ኢኮኖሚው በየዓመቱ በአማካይ በ10.1 በመቶ አድጓል፡፡ ለተመዘገበው ዕድገት የግብርናው ዘርፍ በአማካይ በየዓመቱ በ6.6 በመቶ በማደግ ዋና የዕድገት ምንጭ ሆኗል፡፡ የተገኘው የኢኮኖሚ ዕድገት ታቅዶ ከነበረው የ11 በመቶ ግብ በመጠኑ ዝቅ ያለ ቢሆንም ከብዙ መመዘኛዎች አንጻር ሲታይ እጅግ ፈጣን የሚባል ነው (ሠንጠረዥ 1)፡፡

ሠንጠረዥ-1፡ የኢኮኖሚ ዕድገት በክፍለተ-ኢኮኖሚ (በ2003 በጀት ዓመት በቋሚ ዋጋ)

ክፍላተ ኢኮኖሚ	2003	2004	2005	2006	አማካይ		ትንቢያ
					2003-2006	1996-2006	2007
የጠቅላላ የአገር ዉስጥ ምርት(GDP)	11.4	8.7	9.8	10.3	10.1	10.9	11.4
ግብርና	9.0	4.9	7.1	5.4	6.6	9.0	8.7
ኢንዱስትሪ	15.0	19.6	24.1	21.2	20.0	13.8	23.7
አገልግሎት	12.5	9.6	8.9	11.9	10.7	12.2	9.0
ድርሻ በመቶኛ							
ግብርና	44.7	43.1	42.0	40.2	42.5	47.5	
ኢንዱስትሪ	10.5	11.5	13.0	14.3	12.3	11.2	
አገልግሎት	45.5	45.9	45.6	46.2	45.8	42.4	

በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን አራት ተከታታይ ዓመታት ሶስቱም ክፍላተ ኢኮኖሚዎች ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) የነበራቸው ድርሻ በኢኮኖሚው ውስጥ በመጠኑም ቢሆን መዋቅራዊ ለዉጥ እየታየ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ይኀውም በ2003 በጀት ዓመት ግብርናዉ ከአጠቃላይ የሀገር ዉስጥ ምርት (GDP) 44.7% የሚሸፍን ሲሆን፣ በ2006 ወደ 40.2% ወርዷል፡፡ የኢንዱስትሪ ዘርፉም በአንጻሩ መጠነኛ መዋቅራዊ ለዉጥ ያመጣ ሲሆን፣ በ2003 ከነበረበት 10.5% ድርሻ በ2006 በጀት ዓመት ወደ 14.3% ከፍ ብሏል፡፡ ይህም ሃገራችን ከተያያዘችዉ የኢንዱስትሪ ልማትን የማፋጠን ግብ አንፃር የሚጠበቅ ቢሆንም፣ አሁንም የኢንዱስትሪው በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፍ ድርሻ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ከተቀመጠው ግብ አንፃር ዝቅተኛ

እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል በአገልግሎት ዘርፉ ላይ መጠነኛ ጭማሪ የታየ ሲሆን፣ ይህም በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 45.5% ድርሻ በ2006 በጀት ዓመት ወደ 46.2% ከፍ ብሏል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት አስራ አንድ ዓመታት (1996-2006) የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በየዓመቱ በአማካይ በ10.9 በመቶ አድጓል፡፡ ይህም የሚያሳየው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከጊዜ ወደ ጊዜ ግዙፍ ኢኮኖሚ እየሆነ መምጣቱንና አስተማማኝና ዘለቄታ ያለው የዕድገት ጉዞ (Trajectory) ውስጥ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ ስለሆነም ባለፉት አስርት ዓመታት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የተመዘገበበት፣ የግብርናው ዘርፍ /በተለይም የሰብል ዘርፍ/ ዋናው የዕድገት ምንጭ እንደነበር እና የአገልግሎት ዘርፍም እንደዚሁ ከፍ ያለ ዕድገት የታየበት ነበር፡፡ በሌላ በኩል በዚሁ ወቅት የኢኮኖሚ መዋቅሩ መጠነኛ ሽግግር የታየበት ሲሆን፣ በተለይም ከግብርና ወደ አገልግሎት እና ኢንዱስትሪ መጠነኛ ሽግግር ታይቷል፡፡ የተገኘውን ለውጥ ለማስቀጠልም የግብርና ምርታማነትን በቀጣይም ማጎልበት የሚያስፈልግ ሲሆን፣ መዋቅራዊ ለውጡን ለማፋጠንም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪን ማስፋፋት የሚጠይቅ ሆኗል፡፡

2.2 የዋጋ እንቅስቃሴ

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ የመጀመሪያዎቹ ሁለት የትግበራ ዓመታት ፈታኝ ሆነዉ ከነበሩ ጉዳዮች አንዱ የዋጋ ንረት እንደነበረ ይታወሳል፡፡ የአጠቃላይ ወርሃዊ የዋጋ ንረቱ በ2004 በጀት ዓመት ከ40 በመቶ በላይ ሆኖ የተመዘገበበት ሲሆን፣ የምግብ የዋጋ ንረት ከ50 በመቶ በላይ ደርሶ እንደነበረ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የተከሰተዉ የዋጋ ንረት በኢኮኖሚ ዕድገቱ እና በኑሮ ላይ ጫና እንዳይፈጥር በመንግስት በኩል አስፈላጊ የፖሊሲና አስተዳደራዊ እርምጃዎች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

በዚህም ምክንያት ከ2005 በጀት ዓመት ጀምሮ የዋጋ ንረቱ በከፍተኛ መጠን ሲቀንስ በተለይም በ2006 በጀት ዓመት መጨረሻ የወርሃዊ ዋጋ ዕድገቱ ወደ 8.5 በመቶ ወርዷል፡፡ የምግብ ነክና ምግብ ነክ ያልሆኑ የፍጆታ ዕቃዎች ዋጋዎችም እንዲሁ በቅደም ተከተል ወደ 6.2 በመቶና 11.0 በመቶ ወርዷል (ሠንጠረዥ 2 እና ግራፍ 1)፡፡ የዋጋ ንረቱ በያዝነዉ በ2007 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ዘጠኝ ወራትንም ጨምሮ ላለፉት 23 ወራት በአንድ አሃዝ ተወስኖ የቀጠለ ከመሆኑና መንግስትም

በጉዳዩ ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ የዋጋ መረጋጋቱ ሰፍኖ እንዲቆይ ከሚያደርገዉ ጥረት አንጻር የዋጋ መረጋጋቱ ቀጣይነት እንደሚኖረው አመላካች ነው፡፡

ሠንጠረዥ-2፡ የዋጋ ግሽበት ሁኔታ (Inflation rate)

ወራት	የ12 ወራት ተንከባላይ አማካይ የዋጋ ዕድገት (12 Months Moving Average Inflation)			ወርሃዊ የዋጋ ዕድገት (Year-on-Year Inflation)		
	አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት	የምግብ የዋጋ ግሽበት	ምግብ ነክ ያልሆኑ የዋጋ ግሽበት	አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት	የምግብ የዋጋ ግሽበት	ምግብ ነክ ያልሆኑ የዋጋ ግሽበት
ሰኔ 2003	18.1	15.7	21.8	38.1	45.3	27.9
ሰኔ 2004	33.7	41.7	22.2	20.9	21.5	19.8
ሰኔ 2005	13.5	12.6	14.8	7.4	3.7	11.9
ሰኔ 2006	8.1	5.9	10.6	8.5	6.2	11
ሐምሌ 2006	8	5.9	10.3	6.9	5.8	8.2
ነሐሴ 2006	8	6	10.2	7.2	5.2	9.4
መስከረም 2007	7.9	5.9	10	5.8	3.6	7.8
ጥቅምት 2007	7.6	5.5	10	5.4	2.9	8.3
ህዳር 2007	7.4	5.3	9.8	5.9	4.8	7.1
ታህሳስ 2007	7.4	5.6	9.4	7.7	7.1	8.2
ጥር 2007	7.4	5.6	9.4	7.7	7.1	8.2
የካቲት 2007	7.4	6.0	9.0	8.2	9.6	6.8
መጋቢት 2007	7.4	6.3	8.6	8.5	10.1	6.9

ምንጭ፣ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

በአጠቃላይ የዋጋ ንረትን መቆጣጠር የማክሮ ኢኮኖሚዉን ከማረጋጋት አንጻር ከፍተኛ ድርሻ እንዳለዉ የሚታወቅ ሲሆን፣ በመንግስት በኩል በበጀት ዓመቱ ዋጋን ለማረጋጋት አስፈላጊ ናቸዉ የተባሉ የሞኒተሪና የፊስካል ፖሊሲዎች ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም የንግድ ስርዓቱን ዘመናዊና ቀልጣፋ ለማድረግ እንዲቻል የተጀመሩ ተግባራት ተጠናክረዉ መቀጠልም ይኖርባቸዋል፡፡ የእነዚህ ማሻሻያዎች ተጠናክሮ መቀጠል፣ የግብርና ምርት አቅርቦት ዕድገት እና የሸቀጦች በዓለም ገበያ ዋጋ መረጋጋት፣ በ2007 በጀት ዓመት የዋጋ ሁኔታዉ ተረጋግቶ እንዲቀጥል የሚያስችሉ ናቸዉ፡፡ ሆኖም ለዋጋ መረጋጋት ዘላቂዉ መፍትሔ የግብርና ምርታማነትን ማሳደግ እና የማኑፋክቸሪንግ ምርቶችን ማስፋፋት መሆኑን በአትኩሮት መረዳት አስፈላጊ ነዉ፡፡

ግራፍ 1፡ የፍጆታ ዕቃዎች ዋጋ ዕድገት



2.3 የወጪና ገቢ ንግድ አፈጻጸም

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከፍተኛ ግምት ከተሰጣቸው ዘርፎች መካከል የውጪ ንግድ ዘርፉ አንዱ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በዚህ ረገድ የውጪ ንግድን በማስፋፋት ለኢኮኖሚ ዕድገቱ የጎላ ሚና እንዲጫወት ለማድረግ ዕቅድ ተይዟል፡፡ በዚህም በርካታ የወጪ ምርቶችን ለዓለም ገበያ ማቅረብ የተቻለ ሲሆን፣ በ2003፣ በ2004፣ በ2005 እና በ2006 በቅደም ተከተል 2.7፣ 3.2፣ 3.1፣ እና 3.2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡ የኤክስፖርት ዘርፍ ገቢ አፈጻጸም በ2003 እና በ2004 በቅደም ተከተል የ37.1 እና የ14.8 በመቶ ዕድገት ያስመዘገበ ሲሆን፣ በ2005 በጀት የ4.3 በመቶ ቅናሽ ሲያሳይ፣ በ2006 የ6.8 በመቶ ዕድገት አስመዝግቧል፡፡ በመሆኑም በኤክስፖርት ዘርፍ ምንም እንኳን በዕቅዱ የመጀመሪያ የትግበራ ዓመት (2003 ዓ.ም) ከፍተኛ ውጤት የተገኘ ቢሆንም በ2004፣ በ2005 እና 2006 በጀት ዓመታት ከዘርፉ የተፈለገውን ውጤት ያህል ሊገኝ አልተቻለም (ሠንጠረዥ 3)፡፡

ሠንጠረዥ-3፡ የወጪ ዕቃዎች ንግድ አፈጻጸም (በሚሊዮን ዶላር)

ክፍላተ-ኢኮኖሚ	2003	2004	2005	2006	አማካይ 2003-2006
የዕቃዎች የወጪ ንግድ	2747.1	3152.7	3018.1	3223.9	3035.5
ዕድገት በመቶኛ	37.1	14.8	-4.3	6.8	13.6

በ2003 በጀት ዓመት የወጪ ንግድ አፈጻጸም ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት የነበረው ድርሻ 17 በመቶ ደርሶ የነበረ ሲሆን በ2004፣ በ2005 እና 2006 በቅደም ተከተል ወደ 13.9 በመቶ፣ 12.7 በመቶ፣ እና 11.7 በመቶ አሽቆልቁሏል (ግራፍ 2)፡፡ ይህም የውጪ ንግድ ዘርፉ ዕድገት ከአገር ውስጥ ምርት(GDP) ዕድገት ያነሰ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ለዚህም እንደ ዋና ምክንያት የተወሰደው የወጪ ምርቶችን በበቂ መጠን እና ዓይነት ለገበያ ለማቅረብ ያለው አቅም አሁንም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘቱ ነው፡፡ በሌላ በኩል የተወሰኑ የወጪ ምርቶቻችን ላይ በተለይም ቡና እና ወርቅ የዓለም ገበያ ዋጋ በመቀዛቀዙ ለየዓመቱ የተያዘው የወጪ ምርቶች ገቢ ዕቅድን ማሳካት ባለመቻሉ መሆኑ የሚጠቀስ ነው፡፡

በአንድ በኩል የወጪ ምርቶች አፈጻጸም መቀዛቀዝ እና በሌላ በኩል ለልማቱ ከውጭ ለምናስገባቸው የገቢ ምርቶች የሚከፈለው ክፍያ (Import bill) ከፍ ማለት የንግድ ሚዛኑ ጉድለት የሰፋ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ 2006 በጀት ዓመት የውጪ ንግድ (Export) ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) ድርሻው 11.7 በመቶ ሲሆን፣ የገቢ ንግድ (Import) በአንጻሩ 29.5 በመቶ በመሆኑ የውጭ ንግድ ሚዛኑ ጉድለቱ 17.8 በመቶ ሆኗል፡፡ በአጠቃላይ የወጪ ንግድ አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆንና የገቢ ንግድ ዕድገት ማሳየቱ የወጪና የገቢ ንግድ ሚዛኑ እየሰፋ እንዲሄድ አድርጓል፡፡ ስለሆነም የወጪ ንግድ መስፋፋት ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት የሚኖረው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ የውጭ ምንዛሬን ለማሳደግ እየተደረገ ያለው ጥረት ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

ግራፍ 2 ፡ የወጪና ገቢ ንግድ አፈጻጸም ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት በመቶኛ



2.4 የገንዘብ እንቅስቃሴ አፈጻጸም

የኢትዮጵያ መንግስት የገንዘብ ፖሊሲ ዋነኛ ዓላማዎች የማክሮ ኢኮኖሚውን ማረጋጋት፣ የኢኮኖሚ ዕድገቱን ቀጣይነት ማረጋገጥ፣ የተረጋጋ የውጭ ምንዛሬ ተመን እንዲኖር ማድረግ እና ጤናማ የፋይናንስ ሥርዓትን ማስፈን ናቸው፡፡ ይህንንም ለማስፈጸም የገንዘብ ፖሊሲው በዋናነት የብሔራዊ ባንክ መጠባበቂያ ገንዘብ (Reserve money) ዕድገትን በመቆጣጠር በኢኮኖሚው ውስጥ ሊኖር የሚገባውን የገንዘብ ሥርጭት መጠን መወሰን ነው፡፡

በዚህ ረገድ ከ2003-2006 ባሉት ዓመታት ያለው አፈጻጸም ሲታይ የመጠባበቂያ ገንዘብ ዕድገቱ በ2003 በጀት ዓመት 39.7 በመቶ የነበረ ሲሆን፣ በ2004 ከዜሮ በታች 4.4 በመቶ፣ በ2005 በ13.6 በመቶ እና በ2006 ደግሞ በ15.4 በመቶ አድጓል (ሠንጠረዥ 4)፡፡ በተለይም ከ2004 ጀምሮ ተግባራዊ የተደረገው የገንዘብ ፖሊሲ የዋጋ ዕድገትን ለመቆጣጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረጉ የዋጋ ዕድገቱ የተረጋጋ እንዲሆን አስችሏል፡፡ በሌላ በኩል የገንዘብ አቅርቦት ከ2003-2006 ባሉት ዓመታት የ26.9 በመቶ አማካይ ዕድገት ያሳየ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ጊዜ የብድር ክምችት የ30.3 በመቶ አማካይ ዕድገት አሳይቷል፡፡ ከተጣራ የብድር ክምችት ውስጥ የመንግስት ብድር በአማካይ

በ3.7 በመቶ የቀነሰ ሲሆን፣ የሌሎች (የመንግስት የልማት ድርጅቶችና የግሉ ዘርፍ) የተጣራ ብድር በአማካይ በ40.5 በመቶ አድጓል፡፡

ሠንጠረዥ 4፡ የገንዘብ እንቅስቃሴ (Monetary Developments)

ዓይነት	ዕድገት በመቶኛ				
	2003	2004	2005	2006	አማካይ (2003-2006)
የተጣራ የውጭ ምንዛሬ ሀብት/Net Foreign Assets/	104.2	-28.4	14.7	0.09	22.6
የተጣራ የብድር ክምችት/Net Domestic Credit/	29.8	39.5	23.4	28.4	30.3
የመንግስት/Net Credit to Government/	-13.2	-24.8	1.9	21.2	-3.7
የሌሎች/Net Credit to Other Sectors/	49.7	56.7	26.2	29.2	40.5
የገንዘብ አቅርቦት /Broad Money/	26.6	30.3	24.2	26.5	26.9
የብሔራዊ ባንክ ሪዘርቭ ገንዘብ /Reserve Money/	39.7	-4.4	13.6	18.7	16.9

ምንጭ፡ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ

2.5 የፊሲካል ፖሊሲና የመንግሥት ፋይናንስ አፈፃፀም

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ተግባራዊ የሆነው የፊስካል ፖሊሲ የታክስ ገቢን በማሳደግ እና በወጪ ረገድ በካፒታል ኢንቨስትመንት እና ድህነትን በመቀነስ ረገድ ቁልፍ ሚና ባላቸው ዘርፎች ላይ የበጀት ድልድሉ ቅድሚያ እንዲያገኙ በማድረግ መርህ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የፊስካል ፖሊሲው ዓላማም የወጪ በጀትን በሂደት በሀገር ውስጥ ገቢ በመሸፈን እና የበጀት ጉድለት ዝቅተኛ እንዲሆን በማድረግ ለዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ምቹና የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ ማስፈን ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በበጀት ዓመታቱ በሥራ ላይ ያለውን የታክስ ፖሊሲ እና አስተዳደር ስርዓቱን ይበልጥ በማሻሻል የሀገር ውስጥ ገቢን በማሳደግና ለልማት የሚያስፈልገውን ፋይናንስ በውስጥ አቅም ለመሸፈን እየተደረገ ያለውን ጥረት በማስቀጠል ረገድ አበረታች ውጤት የተመዘገበባቸው ዓመታት ናቸው፡፡ አጠቃላይ የመንግስት ወጪ በአብዛኛው የዕድገት መሠረት የሆኑ የሰው ሀብት ማጎልበትና የመሠረተ ልማት ማስፋፋት ላይ የዋለ ነው፡፡ እንዲሁም በበጀት ዓመታቱ የበጀት ጉድለቱ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ላይ እንደተመለከተው ከአጠቃላይ ኢኮኖሚው ከ3 በመቶ

እንዳይበልጥ በማድረግ ጥብቅ የፊስካል ፖሊሲ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የመንግስት ፋይናንስ አፈጻጸም ዝርዝር በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

2.5.1 ሀገራዊ ጠቅላላ የመንግሥት ገቢ አፈፃፀም

ባለፉት አራት የበጀት ዓመታት የመንግስት ጠቅላላ ገቢ ዕርዳታን ጨምሮ በየዓመቱ በአማካይ 24.5 በመቶ ዕድገት ተመዝግቧል፡፡ በ2006 በጀት አመት የተሰበሰበው የመንግስት ገቢ ዕርዳታን ጨምሮ ብር 158.1 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን፣ ይህም ለዓመቱ በዕቅድ ከተያዘው የ96.7 በመቶ አፈፃፀም አሳያቷል (ሠንጠረዥ 5)፡፡ በተመሳሳይ የ2006 በጀት ዓመት ጠቅላላ የመንግስት ገቢ አፈጻጸም እርዳታን ጨምሮ ከ2005 በጀት ዓመት አፈፃፀም ጋር ሲነጻጸር በ15.2 በመቶ ብልጫ አለው፡፡ ከዚህም ዕድገት ውስጥ ትልቁን ድርሻ የሚይዘው ከታክስ የተሰበሰበው ገቢ መሆኑንም መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ሠንጠረዥ 5. ጠቅላላ የመንግስት ገቢ (በቢሊዮን ብር)

አመልካቾች	2003	2004	2005	2006				ከ2003-2006 የአፈጻጸም አማካይ የዕድገት መጠን	የ2007 ግብ
				ዕቅድ	አፈጻጸም	አፈጻጸም			
						ከዕቅዱ በመቶኛ	ከ2005 አፈጻጸም		
ጠቅላላ ገቢ ዕርዳታን ጨምሮ	**85.6**	**115.7**	**137.2**	**163.5**	**158.1**	**96.7**	**15.2**	**24.5**	173.0
ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ	69.1	102.9	124.1	147.7	146.2	99.0	17.8	28.9	145.3
የታክስ ገቢ	59.0	85.7	107.0	133.3	133.1	99.8	24.4	32.7	127.2
ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች	10.1	17.1	17.1	14.4	13.1	90.9	-23.5	10.3	18.1
የውጭ ዕርዳታ	16.5	12.8	13.1	15.8	11.9	75.5	-9.2	1.0	27.7

የአገር ውስጥ ገቢ

በ2006 በጀት አመት ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ገቢ ብር 146.2 ቢሊዮን ተሰብስቧል፡፡ የ2006 አፈጻጸም ከ2005 አፈጻፀም ጋር ሲነፃፀር የ18 በመቶ ዕድገት አለው፡፡ ከዚህ የገቢ ዘርፍ በአራት አመቱ ውስጥም በአማካይ በየአመቱ የ28.9 በመቶ ዕድገት ተመዝግቧል:: በ2006 በጀት ዓመት የአገር ውስጥ ገቢው ከጠቅላላ የመንግስት ገቢ ያለው ድርሻ 92.5 በመቶ የሚይዝ ሲሆን፣ ይህም በ2003፣ በ2004፣ እና በ2005 በጀት አመታት እንደ ቅደም ተከተላቸው ከተመዘገበው የ80.7፣

የ90.4 እና የ88.9 በመቶ ድርሻ ጋር ሲነፃፀር እጅግ ከፍ ያለ ነው፡፡ የባለፉት አራት ዓመታት የአገር ውስጥ ገቢ አፈፃፀም ዕድገት ከማሳየቱም ባሻገር ከጠቅላላ የመንግስት ገቢ ያለው ድርሻ እየላቀ የመጣ መሆኑንና የመንግስት ፋይናንስ ከጊዜ ወደ ጊዜ በራስ አቅም ላይ እየተመሰረተ መምጣቱን ያሳያል፡፡

የታክስ ገቢ

በ2006 በጀት ዓመት ከታክስ ገቢ ብር 133.1 ቢሊዮን ገቢ የተሰበሰበ ሲሆን፣ ይህም ለበጀት አመቱ ከተያዘው ዕቅድ የ99.8 አፈፃጸም ያሳያል፡፡ እንዲሁም የበጀት ዓመቱ አፈጻጸም ከ2005 አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር በ24 በመቶ በማደግ ከፍተኛ ዕድገት አሳይቷል፡፡ በ2006 በጀት ዓመት ከታክስ የገቢ ምንጭ የተሰበሰበው ገቢ ከጠቅላላ የመንግስት ገቢ ውስጥ 84.2 በመቶ ድርሻ የሚይዝ ሲሆን፣ ይህም በ2003፣ በ2004፣ እና በ2005 እንደ ቅደም ተከተላቸው ከተመዘገበው የ69፣ የ74.1 እና የ78 በመቶ ድርሻ ጋር ሲነፃፀር እጅግ ከፍ ያለ ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው የመንግስት ገቢ በአብዛኛው አሰባሰቡ በአስተማማኙ የመንግስት የገቢ ምንጭ ላይ እየተመሰረተ መምጣቱን የሚያመለክት ነው(ግራፍ 3)፡፡

ግራፍ 3. ከ2003-2006 በጀት ዓመታት የታክስ ገቢ ከጠቅላላው የመንግስት ገቢ ያላቸው ድርሻ በመቶኛ



በአጠቃላይ በ2006 የበጀት አመት ከታክስ የተሰበሰበው ገቢ ከፍተኛ ዕድገት የታየበት ቢሆንም ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት አንጻር ሲታይ ክንውኑ ከዕቅዱ ዝቅ ያለ ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ 12.7 በመቶ የደረሰ ሲሆን፣ በ2005 የበጀት ዓመት ድርሻው 12.4 በመቶ ያህል ነበር (ሠንጠረዥ 6)፡፡ ይህም የታክስ ገቢው ዕድገት ከኢኮኖሚው ዕድገት ጋር በተመጣጣኝ ባለመጨመሩ ምክንያት እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ሊደረስበት ከታቀደው የ15 በመቶ የአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ አንጻር ሲታይ ተጨማሪ የታክስ አስተዳደር ጥረት መደረግ እንዳለበት አመላካች ነው፡፡ በተጨማሪም በተመሳሳይ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ ከሚገኙ ከሰሀራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሀገራት አማካይ አፈጻጸም (17 በመቶ) ላይ ለመድረስም በታክስ አስተዳደርና አሰባሰብ ተጨማሪ ጥረት መደረግ እንዳለበት ያመለክታል፡፡

ሠንጠረዥ 6. ጠቅላላ የመንግስት ገቢ ከጠ/የሀገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ ያላቸው ድርሻ በመቶኛ

አመልካቾች	2003	2004	2005	2006		ከ2003-2006 የአፈጻጸም አማካይ	የ2007 (GTP) ግብ
				ዕቅድ	አፈጻጸም		
ጠቅላላ ገቢ ዕርዳታን ጨምሮ	**16.6**	**15.5**	**15.9**	**16.4**	**15.1**	**15.8**	**20.4**
ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ	*13.4*	*13.8*	*14.3*	*14.8*	*14.0*	*13.9*	*17.1*
የታክስ ገቢ	*11.5*	*11.5*	*12.4*	*13.3*	*12.7*	*12.0*	*15*
ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች	*2.0*	*2.3*	*2.0*	*1.4*	*1.2*	*1.9*	*2.1*
የውጭ ዕርዳታ	*3.2*	*1.7*	*1.5*	*1.6*	*1.1*	*1.9*	*3.3*

ለታክስ ገቢው በየአመቱ መሻሻል የኢኮኖሚ ዕድገት እና የታክስ አስተዳደር ስርዓቱን ለማጠናከር እየተወሰደ ያለው እርምጃ ዋና ተጠቃሾች ናቸው፡፡ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የታክስ ገቢ ግቦችን ከማሳካት አንጻር አራት ዋና ዋና ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ እነሱም ዘመናዊ የታክስ መረጃ ሥርዓትን ማጠናከር፣ የደንበኞች ትምህርትና ግንኙነትን ማሳደግ፣ የታክስ ህግን ማስከበር እና የታክስና ገቢዎች መዋቅር ተቋማዊ አቅም ማሳደግ ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር ባለፉት አራት የዕቅድ

ዓመታት የተከናወኑ ሥራዎች ውጤት ማስመዝገብ የጀመሩ ቢሆንም፣ በቀጣይም አጠናክሮ በመተግበር የታክስ ገቢውን ለማሳደግ ተጨማሪ ጥረት ማድረግ እንደሚያሻ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች

በ2006 በጀት ዓመት ታክስ ካልሆኑ ምንጮች ብር 13 ቢሊዮን ገቢ ተሰብስቧል፡፡ ከዚህ ገቢ ትልቁን ድርሻ የሚይዙት ከመንግስት ኢንቨስትመንት ገቢ፣ ከመንግስት ዕቃ እና አገልግሎቶች ሽያጭ፣ ከፈቃድና ሌሎች ክፍያዎች እንዲሁም ከከተማ ቦታ የሊዝ ክፍያዎች የተሰበሰበ ገቢ ነው፡፡

የውጭ አገር ዕርዳታ

ለ2006 በጀት ዓመት ከታ ቀደው ሌላው የገቢ ምንጭ ከልማት አጋሮች በመሰረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ የሚገኘው የውጭ ሀብት ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ ብር 2.5 ቢሊዮን ገቢ በዕርዳታ መልክ የተገኘ ሲሆን፣ በብድር መልክም ብር 6.1 ቢሊዮን ተገኝቷል፡፡ በአጠቃላይ በ2006 በጀት ዓመት ከውጭ አገር ዕርዳታ ብር 11.9 ቢሊዮን ገቢ ተገኝቷል፡፡ ይህም የፋይናንስ ምንጭ በአብዛኛው የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ከማሳካት አንፃር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላላቸው የወጪ ዘርፎች የሚመደብ የፋይናንስ አይነት ነው፡፡ ሆኖም ከአጠቃላይ የመንግስት የፋይናንስ ምንጭ የዕርዳታ ድርሻ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ የመጣና ወጪን በአገር ውስጥ የመሸፈን አቅም እየተሻሻለ መምጣቱን መገንዘብ ይቻላል፡፡

2.5.2 ሀገራዊ የመንግሥት ወጪ አፈፃፀም

የመንግሥት የበጀት ድልድል በዋነኝነት ዕድገትን በሚያፋጥኑና ድህነትን ለመዋጋት ቁልፍ ሚና ባላቸው ዘርፎች ላይ የሚያተኩር ሆኖ የመደበኛ ወጪን ከሀገር ውስጥ ከሚሰበሰብ ገቢ የመሸፈን እና የካፒታል ወጪን ደረጃ በደረጃ ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ ገቢ ለመሸፈን የሚያስችል መርህን የተከተለ ነው፡፡ የባለፉት አራት የዕቅድ ዓመታት የመደበኛ ወጪ ፍላጐት ታሳቢ ካደረጋቸው ጉዳዮች ያለፈው በጀት ዓመት አፈጻጸም፣ የቀጣዩ በጀት ዓመት የአገልግሎት መስፋፋት እና የዋጋ ንረት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ የካፒታል ወጪ ፍላጐትን በተመለከተ በመካሄድ ላይ ላሉ ነባር ፕሮጀክቶች ቅድሚያ በመስጠትና በመንግሥት ፖሊሲና ስትራቴጂ ትኩረት የተሰጣቸው የተመረጡ አዳዲስ ፕሮጀክቶች እንዲካተቱ በማድረግ ለማስተናገድ ጥረት ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የካፒታል

ወጪዎች በግብርና ልማት፣ በምግብ ራስን ማስቻል፣ ውሃ፣ ትምህርት፣ ጤና፣ መንገድ፣ የገጠር ኤሌክትሪክ መስፋፋትና አገልግሎት ማዳረስ ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት እንዲደለደሉ ተደርጓል፡፡

ሠንጠረዥ 7፡ ሀገራዊ የመንግስት ወጪ አፈጻጸም /በቢሊዮን ብር/

አመልካቾች	2003	2004	2005	2006				ከ2003-2006 የአፈጻጸም አማካይ የዕድገት መጠን	የ2007 ግብ
				ዕቅድ	አፈጻጸም	አፈጻጸም			
						ከዕቅዱ በመቶኛ	ከ2005 አፈጻጸም		
ጠቅላላ ወጪ	**93.8**	**124.4**	**154.0**	**194.3**	**185.5**	**95.4**	**20.4**	**26.5**	201.1
መደበኛ ወጪ	40.5	51.4	62.7	82.7	78.1	94.4	24.4	24.5	78.9
የካፒታል ወጪ	53.3	73.0	91.3	111.7	107.4	96.2	17.7	28.2	122.2
የድህነት ተኮር ዘርፍ ወጪ	**62.4**	**87.6**	**107.8**	**133.1**	**126.8**	**95.2**	**17.6**	**27.9**	**146.8**
ትምህርት	23.4	29.8	34.6	44.8	42.5	94.9	22.7		
ጤና	6.3	7.7	11.3	14.8	13.6	91.9	20.4		
ግብርና	8.3	11.1	14.6	15.2	17.7	116.3	20.8		
ውሃ	5.9	10.2	12.7	16.5	14.3	86.7	13.0		
መንገድ	18.5	28.9	34.5	41.7	38.6	92.5	12.0		

ባለፉት አራት የዕቅድ ዓመታት ውስጥ ጠቅላላ የመንግስት ወጪ በአማካይ በየዓመቱ በ26.5 በመቶ እያደገ የመጣ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ በተለይ ለድህነት ተኮር ዘርፎች የዋለው ወጪ በአማካይ በየዓመቱ በ27.9 በመቶ አድጓል (ሠንጠረዥ 7)፡፡ በ2006 በጀት ዓመት የብር 194.3 ቢሊዮን የወጪ በጀት ዕቅድ ተይዞ የነበረ ሲሆን ወጪው ብር 185.5 ቢሊዮን በመሆኑ አፈጻጸሙ የበጀቱን 95.4 በመቶ ሆኗል፡፡ ከዚህ ወጪ ውስጥ 59 በመቶው ለካፒታል ወጪ የዋለ ሲሆን፣ ቀሪው 41 በመቶ ደግሞ ለመደበኛ ወጪ መሸፈኛ ወጪ የተደረገ ነው፡፡

ይህም የወጪ ድልድሉ የፊስካል ፖሊሲውን ተከትሎ ተጨማሪ ሃብት ለሚፈጥሩ የኢንቨስትመንት ሥራዎች የዋለ መሆኑን ያሳያል፡፡ ከ2006 በጀት ዓመት ከጠቅላላ ወጪ ውስጥ 68.4 በመቶው (ብር 126.8 ቢሊዮን) የሚሆነው ድህነትን ለመቅረፍ ትልቅ አስተዋጽኦ ለሚያደርጉ ቅድሚያ ለተሰጣቸው የማህበራዊና የመሠረተ ልማት ፕሮግራሞች ማለትም የትምህርት፣ ጤና፣ ውሃ፣ ግብርናና መንገድ ልማት ኢንቨስትመንት መሸፈኛ እንዲውል ተደርጓል፡፡ ይህም የበጀት አመዳደብ ባለፉት አራት አመታት ከተመዘገበው አፈፃፀም ጋር ተመሳሳይ ሆኗል (ሠንጠረዥ 8)፡፡ ለካፒታል በጀት ዕድገትም

በተለይ ከ2004 የበጀት ዓመት ጀምሮ ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ለማስፈጸም በፌዴራል መንግስት ለክልሎች የተመደበው የማጠናከሪያ በጀት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረጉ ነው፡፡ ይህ የወጪ አመዳደብ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ለማሳካትና ድህነትን ለማስወገድ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

ሠንጠረዥ 8፣ የ2006 በጀት ዓመት የመደበኛ፣ የካፒታል ወጪ እና ጠቅላላ የድህነት ተኮር ዘርፎች ወጪ ከጠቅላላ የመንግስት ወጪ ያለው ድርሻ በመቶኛ

አመልካቾች	2003	2004	2005	2006	ከ2003-2006 አማካይ
መደበኛ ወጪ	43.2	41.3	40.7	42.1	41.8
የካፒታል ወጪ	56.8	58.7	59.3	57.9	58.2
የድህነት ተኮር ዘርፍ ወጪ	66.5	70.4	70.0	68.4	68.8

በአጠቃላይ ሲታይ የኢትዮጵያ በጀት አመዳደብ ለካፒታል በጀት ትልቁን ድርሻ የሚመደብበት ሲሆን፣ ይህም ከሌሎች በእድገት ደረጃቸው ከኢትዮጵያ ተቀራራቢና ከሌሎች በማደግ ላይ ካሉ አገሮች ከሚታየው የሀብት አመዳደብ መርህ አንፃር ሙሉ በሙሉ የተለየ ነው (ሠንጠረዥ 9)፡፡ ይህ የበጀት አመዳደብ የኢትዮጵያ መንግስት ለልማት ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው፡፡ በቀጣዩ የዕቅድ ዘመን ይህ የበጀት አመዳደብ በዚሁ መርህ ተቃኝቶ ይቀጥላል ተብሎ ይታመናል፡፡

ሠንጠረዥ 9፣ የኢትዮጵያ የመደበኛና የካፒታል ወጪ አመዳደብ ከጎረቤት አገሮች እና ከሌሎች በማደግ ላይ ካሉ አገሮች ንጽጽር በ2006 ዓ.ም

አገሮች	የካፒታል በጀት ድርሻ ከጠቅላላው በጀት	የመደበኛ በጀት ድርሻ ከጠቅላላው በጀት
የኢትዮጵያ	58%	42%
ሩዋንዳ	48%	52%
ኬንያ	27%	73%
ታንዛንያ	31%	69%
ጋና	20%	80%
ቬትናም	32%	68%

ምንጭ፣ የየሀገራቱ የገንዘብ ሚኒስቴር ድህረ-ገጽ

በሌላ በኩል የበጀት አጠቃቀሙ በውጤታማነትና በቁጠባ ላይ የተመሰረተ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ከመዘርጋት አንጻር ከበርካታ ዓመታት በፊት ስራው የተጀመረው የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ሪፎርም ፕሮግራም በተጠናከረ ሁኔታ ተግባራዊ እየተደረገ ነው፡፡ በተለይም በቅርቡ ተግባራዊ የተደረገውና በጀትን ከውጤት ጋር ለማስተሳሰር ያስቻለው የፕሮግራም በጀት አሠራር ባለፉት በጀት ዓመታት ሙሉ ለሙሉ በፌደራል መሥሪያ ቤቶች ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

2.5.3 የበጀት ጉድለት

ከፊስካል ፖሊሲ አፈፃፀም አንፃር ያለፉት የዕቅድ አመታት የዋጋ ንረት ለመቆጣጠር የመንግስት ገቢና ወጪን በማመጣጠንና የበጀት ጉድለቱንም የዋጋ ግሽበትን በማያስከትል የብድር አይነቶች በመጠቀም የተሸፈነ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የበጀት ጉድለቱ ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2003፣ በ2004፣ በ2005 እና በ2006 በጀት ዓመት በቅደም ተከተል የ1.6 በመቶ፣ የ1.2 በመቶ፣ የ1.9 በመቶ እና የ 2.6 በመቶ የያዘ ሲሆን፣ ይህም ጥብቅ የፊስካል ፖሊሲ በመተግበር አመታዊ የብድር መጠን ከአጠቃላይ ኢኮኖሚው 3 በመቶ በላይ እንዳይበልጥ የተቀመጠውን ግብ የተከተለ መሆኑን ነው፡፡ የ2006 የበጀት ጉድለት ብር 26.9 ቢሊዮን የነበረ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ 74.8 በመቶ ያህሉ ከውጭ ሀገር በተገኘ የተጣራ ብድር፣ 25.2 በመቶ ያህሉ ደግሞ ከሀገር ውስጥ በተገኘ የተጣራ ብድር የተሸፈነ ነው፡፡

3. የ2007 በጀት ዓመት የአጠቃላይ ኢኮኖሚና ፊሲካል አፈፃፀም ዕይታ

3.1 የአጠቃላይ ኢኮኖሚ አፈጻጸም

የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የመጨረሻ ዓመት በሆነው በያዝነው የ2007 በጀት ዓመት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የ11.4 በመቶ ዕድገት እንደሚያስመዘግብ የተተነበየ ሲሆን ዕድገቱም በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች በግብርናው፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች እንደሚመዘገብ ይገመታል:: ለኢኮኖሚው ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ያለውን የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ አፈጻጸም የሚያመለክቱ መረጃዎች በቅርቡ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን ይፋ አድርጓል። ባለሥልጣኑ በአርሶ አደር ግብርና ረገድ የመኸር የግብርና ሰብል ድህረ ምርት ዳሰሳ ጥናት ያደረገ ሲሆን፣ በ2007 በጀት ዓመት በድምሩ 270.3 ሚሊዮን ኩንታል የመኸር ዋና ዋና የምግብ ሰብሎች ምርት ከአርሶ አደር መሬት እንደሚሰበሰብ የጥናቱ ትንበያ አመልክቷል። ይህም በ2006 ከተሰበሰበው ተመሳሳይ የመኸር ምርት ጋር ሲወዳደር የ7.47 በመቶ ዕድገት እንደሚኖረው ያሳያል።

የኢንዱስትሪ ዘርፍ የ2007 ትክክለኛ አፈጻጸም የሚያሳዩ መረጃዎች የሚደርሱት የበጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ቢሆንም በዘርፉ ከሚታየው እንቅስቃሴ አንፃር ኢንዱስትሪ በበጀት ዓመቱ ፈጣን ዕድገት እንደሚያስመዘግብ ተገምቷል። በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከታቀፉት መካከል ዋነኞቹ የማኑፋክቸሪንግ እና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪዎች ናቸው። በበጀት ዓመቱ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በላቀ ፍጥነት እንዲያድግ ለማድረግ የወጡትን ስትራቴጂዎች በላቀ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ነው። የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በዋናነት በግሉ ዘርፍ የሚከናወን እንደመሆኑ መጠን በዘርፉ የሚደረገው የአገር ውስጥና የውጪ ኢንቨስትመንት ፍሰት በከፍተኛ መጠን እንዲጨምር ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ነው። በግሉ ዘርፍ እየተደረገ ያለው ኢንቨስትመንት በተጠናከረ ሁኔታ እንዲቀጥል እየተደረገ ያለው ድጋፍ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። የኢንዱስትሪውን ዕድገት ለመደገፍ ለግል ኢንቨስትመንት መስፋፋት ማነቆ ናቸው ተብለው የተለዩትን የመሬት አቅርቦት፣ የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥና ፋሲሊቴሽን፣ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ችግሮችን ለመቅረፍ ጥረት እየተደረገ ይገኛል። በዚህም የማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፍ ተጠናክሮ ለኢንዱስትሪ ዕድገቱ የተሻለ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ይጠበቃል። በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በተለይም በመንግስት የሚካሄዱ ትልልቅ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ፣ ወጪና የጥራት ደረጃ እንዲጠናቀቁ ለማድረግ ርብርብ እየተደረገ በመሆኑ በመልካም አፈጻጸም ደረጃ ላይ ይገኛሉ ብሎ መገመት ይቻላል። በግሉ ዘርፍ

የሚካሄዱት የኮንስትራክሽን ሥራዎችም ቢሆን እንቅስቃሴያቸው በመልካም ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ ስለዚህም በቀሪዎቹ ወራት አስፈላጊው ርብርብ ከተደረገ የኢንዱስትሪው ዘርፍ ዕድገትም ተስፋ የሚጣልበት ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

በአገልግሎት ዘርፍ የታቀፉ ንዑስ ዘርፎችም በያዝነው በጀት ዓመት ዕድገት ማስመዝገብ እንደሚቀጥሉ ይጠበቃል፡፡ በአገልግሎት ክፍለ-ኢኮኖሚው ውስጥ የጅምላና ችርቻሮ፣ የሪል ኢስቴት፣ የመሳሪያ ኪራይና ተያያዥ ንግዶች፣ የትራንስፖርትና ኮሙኒኬሽን እንዲሁም የሆቴልና ሬስቶራንት የመሳሰሉት ዋና ዋና ንዑስ ዘርፎች ለዘላቂ ዕድገቱ በጎ ሚና መጫወት እንዲችሉ ለማድረግ የወጡትን የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድ እና አሠራር ህጎች በተሟላ ሁኔታ የሚደረገው ተፈፃሚነት ዘርፉን ይበልጥ ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ ዕድገቱ ቀጣይ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ ይህም እንዲረጋገጥና ለዕድገቱ የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ በቀሪዎቹ ወራት በብቃት መምራት ይጠይቃል፡፡ በመንግስት በኩል የሚካሄዱ የትምህርት፣ የጤናና የቴሌኮሙኒኬሽን የመሳሰሉት አገልግሎቶች ልማት በአስተማማኝ ሁኔታ ተግባራዊ እየተደረጉ በመሆናቸው ለ2007 በዕቅድ የተያዘውን ግብ በማሳካት ለአገልግሎት ዘርፉ የሚያደርጉትን የዕድገት አስተዋጽኦ ማሳካት እንደሚቻል ይታመናል፡፡

በአጠቃላይ በሁሉም ዘርፎች እየታየ ካለው እንቅስቃሴ አንፃር ኢኮኖሚው በ2007 በጀት ዓመትም ለ12ኛ ዓመታት በተከታታይ በፍጥነት ማደጉን እንደሚቀጥል ተገምቷል፡፡ ስለዚህም አሁንም በየዘርፉ የወጡትን ስትራቴጂዎች በወጥነት አሟልቶ ለመተግበር እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡ የኢኮኖሚው ዕድገት ከፍላጎት አንጻርም ያለውን አቅም መፈተሽና መዳሰስ የሚገባ ሲሆን፣ የግል ፍጆታ አፈጻጸም ለኢኮኖሚ ዕድገቱ የራሱ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ በተለይም የዋጋ መረጋጋት በመታየቱና ከኢኮኖሚ ዕድገቱ የገቢ መጨመር ጋር ተያይዞ የግል ፍጆታ ሚዛናዊ በሆነ መልክ ለኢኮኖሚ ዕድገቱ አስተዋጽኦ እያደረገ እንደሆነ ይታመናል፡፡ የመንግስት የፍጆታ ወጪም ከታየው የ2007 በጀት ዓመት የመንግስት ወጪ አፈጻጸም አንጻር በመልካም አፈጻጸም ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ እንዲሁም የኢኮኖሚ ዕድገቱን ለማረጋጋጥ የኢንቨስትመንት አፈጻጸም ወሳኝ ሲሆን፣ ከዚህ አንጻር በመንግስት በኩል የሚደረጉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች በዕቅዱ መሠረት ተግባራዊ እየተደረጉ ናቸው፡፡ የግሉም ኢንቨስትመንት እየተሻሻለ እንዲሄድ አስፈላጊው ድጋፍና ክትትል በመደረግ ላይ ነው፡፡ በአጠቃላይ የ11 በመቶ ዕድገቱን

ለማሳካት የግልና የመንግስት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ማነቆዎችን ለመፍታት የሁሉንም ርብርብ ይጠይቃል፡፡

ሆኖም ከፍላጎት አንፃር የኤክስፖርት ንግድ መቀዛቀዝ በኢኮኖሚ ዕድገቱ ላይ በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚኖረው መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ በ2007 በጀት ዓመት በመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ ወራት ከወጪ ንግድ (ኤክስፖርት) 2,182.8 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ የተገኘ ሲሆን፣ ይህም በ2006 ተመሳሳይ ወቅት ከተገኘው 2,286.9 ሚሊዮን ዶላር የወጪ ንግድ ገቢ ጋር ሲነፃጸር በ104.1 ሚሊዮን ዶላር (በ4.6 በመቶ) ያህል ዝቅ ያለ አፈጻጸም ማሳየቱን የተገኙት መረጃዎች አሳይተዋል፡፡ የዘጠኝ ወራት የኤክስፖርት ገቢው ከአለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ቅናሽ ያሳየ መሆኑም ለኤክስፖርት ገቢ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት እንዳለበት የሚያመላክት ነው፡፡ በመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ ወራት ከዕቃዎች ኤክስፖርት የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ለዓመቱ ከታቀደው ጋር ሲነጻፀር 39.8 በመቶ አፈጻጸም አሳይቷል፡፡ ያለፉት ዘጠኝ ወራት የኤክስፖርት አፈፃፀም ለዓመቱ የተያዘውን የኤክስፖርት ግብ ከማሳካት አንጻር አስቸጋሪ እንደሚሆን ከወዲሁ ያመላከተ ነው፡፡

በአንፃሩ በ2007 በጀት ዓመት በመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ ወራት ለገቢ ንግድ (ኢምፖርት) 16.4 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወጪ የተከፈለ ሲሆን፣ ይህም በ2006 ተመሳሳይ ወቅት ከተከፈለዉ 12.1 ቢሊዮን ዶላር የገቢ ንግድ ጋር ሲነፃጸር በ4.3 ቢሊዮን ዶላር (በ35.7 በመቶ) ያህል ከፍ ያለ ነው፡፡ ለዚህ ከፍተኛ ጭማሪ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች፣ የካፒታል ዕቃዎች እና የትራንስፖርት ዕቃዎችና ግብዓቶች ከፍተኛ ጭማሪ ማሳየታቸዉ ሲሆን፣ ነዳጅና የሞተር ዘይት ላይ ግን ከፍተኛ የሆነ ቅናሽ ታይቷል፡፡ ይህ ዕድገት ከኤክስፖርት ዕድገቱ ጋር ሲነጻጸር በጣም የሚልቅ በመሆኑ የንግድ ሚዛኑ እየሰፋ መሆኑን በግልፅ የሚያመላክት ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ዘጠኝ ወራት ከሸቀጦች የተገኘው የኤክስፖርት ገቢ ለገቢ ዕቃዎች የወጣውን የውጭ ምንዛሪ መሸፈን የቻለው 13.3 በመቶ ያህሉን ብቻ ነው፡፡

የወጪ ንግድ (ኤክስፖርት) አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆንና የገቢ ንግድ (ኢምፖርት) ዕድገት ማሳየቱ የወጪ ንግድ ሚዛኑ እየሰፋ እንዲሄድ አድርጓል፡፡ የወጪ ንግድ መስፋፋት ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት እንደዚሁም ለኢንቨስትመንት መስፋፋት ከፍተኛ ሚና ያለው መሆኑ ይታወቃል፡፡ እንደዚሁም ኢኮኖሚው ደረጃ በደረጃ ከውጭ ዕርዳታና ብድር ጥገኝነት እንዲላቀቅ ለማድረግ

የኤክስፖርት መስፋፋት ወሳኝ ነው፡፡ በአጠቃላይ በ2007 በጀት ዓመት የውጭ ምንዛሪን በዘላቂነት ለማሳደግ ለሚደረገው ጥረት የኤክስፖርት መስፋፋት ዋነኛው አማራጭ ነው፡፡

የዋጋ ዕድገትን በተመለከተ በ2007 በጀት ዓመትም ተግባራዊ የሚደረጉ የፊስካልና የገንዘብ ፖሊሲዎች የተረጋጋ የዋጋ ዕድገት ለማረጋገጥ ያለሙ ናቸው፡፡ እንደዚሁም በያዝነው ዓመት የሰብል ምርት ጭማሪ የተገኘ በመሆኑ ለዋጋ መረጋጋት ትልቅ ሚና ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም በ2007 በጀት ዓመት የሚጠበቀው የአንዳንድ ሸቀጦች የዓለም ገበያ ዋጋ መቀነስ ለአገር ውስጥ የዋጋ መረጋጋት የራሱ አስተዋፅ እንደሚኖረው ይገመታል፡፡ ስለሆነም በ2007 በጀት ዓመት የዋጋ ንረቱ የተረጋጋ ሆኖ እንደሚቀጥል ይጠበቃል፡፡ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ መረጃዎችም ይህንኑ የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ በመጋቢት ወር 2007 ዓ.ም የተመዘገበው የ12 ወራት አማካይ (12 Months Moving Average) አገራዊ አጠቃላይ የዋጋ ዕድገት 7.4 በመቶ ነው፡፡ ይህም ዕድገት ካለፈው ታህሳስ ወር ጀምሮ ተመሳሳይ ሲሆን፣ ላለፉት አስራ ስምንት ተከታታይ ወራትም በነጠላ አሃዝ የተወሰነ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

3.2 የፊሲካል ፖሊሲና የፌዴራል መንግስት ፋይናንስ አፈጻጸም[1]

በ2007 በጀት ዓመት በመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ ወራት ከታክስ፣ ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች፣ የቀጥታ በጀት ድጋፍና ዕዳ ቅነሳን ጨምሮ ብር 109.0 ቢሊዮን ገቢ ተሰብስቧል፡፡ ይህም ከፀደቀው የዓመቱ በጀት ጋር ሲነጻጸር 82.0 በመቶ አፈፃፀም አሳይቷል፡፡ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ዘጠኝ ወራት ዉስጥ የተሰበሰበው መደበኛ ገቢ (ታክስ እና ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች) ብር 100.8 ቢሊዮን ሲሆን ካለፈዉ በጀት ዓመት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር የ17.5 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል (ሠንጠረዥ 5)፡፡ በሌላ በኩል በተመሳሳይ ወቅት ውስጥ ብር 110.9 ቢሊዮን ጠቅላላ ወጪ የተደረገ ሲሆን፣ ይህም ከጸደቀው የዓመቱ በጀት ጋር ሲነጻጸር የ68.0 በመቶ አፈፃፀም አሳይቷል፡፡

3.2.1 የገቢና ዕርዳታ አፈጻጸም

ታክስ ገቢ

በ2007 በጀት ዓመት የመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ ወራት ከበጀት ታሳቢ ከተሰጠ አገልግሎት፣ የክልሎች ድርሻና የቀረጥ ተመላሽ የተሰበሰበውን ብር 9.0 ቢሊዮን ጨምሮ የታክስ ገቢው ብር 92.7 ቢሊዮን

[1] በሚያዝያ ወር የጸደቀውን ተጨማሪ በጀት አያካትትም፡፡

ሲሆን፣ ይህም ለዓመቱ ከተያዘው የብር 115.5 ቢሊዮን ገቢ ዕቅድ የ80.3 በመቶ አፈፃፀም አሳይቷል፡፡ ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ክንውን ጋር ሲነጻጸር ደግሞ የብር 14.9 ቢሊዮን ወይም የ19.2 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ ሆኖም ከዚህ ከተሰበሰበው ጠቅላላ የታክስ ገቢ ውስጥ ለባለበጀት መ/ቤቶች የተሰጠውን ታሳቢ አገልግሎት፣ የክልሎች ድርሻና የቀረጥ ተመላሽ ገቢ ብር ተቀናሽ ሲደረግ፣ የተጣራ የፌዴራል መንግስት ገቢ ብር 83.7 ቢሊዮን ሆኗል፡፡ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ ወራት የተሰበሰበው የተጣራ የታክስ ገቢ ከዓመታዊ ዕቅዱ ያሳየው አፈጻጸም 72.5 በመቶ ሲሆን በ2006 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከታየው አፈጻጸም አንጻር ሲታይ በመጠኑ ከፍ ያለ መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡ ሆኖም ያለፉት ዓመታት የታክስ ገቢ አፈጻጸም መረጃ ሲታይ በየትኛውም የበጀት ዓመት በዕቅድ የተያዘውን የተጣራ የፌዴራል መንግስት ገቢ በሙሉ መሰብሰብ አለመቻሉን መረዳት የሚቻል ነው፡፡

ሠንጠረዥ 5፡ የ2007 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ዘጠኝ ወራት የፌዴራል መንግስት የገቢ አፈጻጸም (በሚሊዮን ብር)

ዝርዝር	**የ2007 ዕቅድ**	**ከሐምሌ - መጋቢት ክንዉን**				**የ9 ወር ክንውን ከፀደቀዉ በጀት**
		2007	**2006**	**ልዩነት ካለፈው በጀት ዓመት**		
		አፈጻጸም	**አፈጻጸም**	**በብር**	**በመቶኛ**	**በመቶኛ**
የመደበኛ ገቢ ቀጥታ የበጀት ድጋፍና ዕዳ ቅነሳ	**132,895.6**	**109,029.2**	**91,639.2**	**17,390.0**	**19.0**	**82.0**
መደበኛ ገቢ	**123,053.1**	**100,761.8**	**85,761.8**	**15,000.0**	**17.5**	**81.9**
የታክስ ገቢ	**115,516.2**	**92,734.9**	**77,826.5**	**14,908.4**	**19.2**	**80.3**
ቀጥታ ታክስ	**29,934.6**	**24,078.1**	**21,509.2**	**2,568.9**	**11.9**	**80.4**
የአገር ዉስጥ ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች	**30,320.2**	**28,699.6**	**22,460.8**	**6,238.8**	**27.8**	**94.7**
ከአገር ዉስጥ ምርት ተ.እ.ታ.	*11,861.2*	9,832.9	8,907.3	925.6	10.4	82.9
የአገልግሎት ተ.እ.ታ.	*13,592.3*	15,565.6	10,554.4	5,011.2	47.5	114.5
ከአገር ዉስጥ ኤክሳይዝ ታክስ	*4,300.0*	2,991.8	2,700.6	291.2	10.8	69.6
የዕቃዎችና የአገልግሎት ተርን ኦቨር ታክስ	*71.0*	18.3	28.3	-10.0	-35.3	25.8
የቴምብር ሽያጭ ቀረጥ	*495.7*	290.9	270.1	20.8	7.7	58.7
የዉጭ ንግድ ቀረጥ	**55,261.3**	**39,957.2**	**33,856.5**	**6,100.7**	**18.0**	**72.3**
የጉምሩክ ቀረጥ	*18,334.4*	13,332.3	11,446.5	1,885.8	16.5	72.7
የገቢ ዕቃዎች ኤክሣይዝ ታክስ	*6,172.1*	4,277.6	3,320.8	956.8	28.8	69.3
የገቢ ዕቃዎች ተጨማሪ እሴት ታክስ	*19,974.1*	14,698.9	12,436.9	2,262.0	18.2	73.6
ሱር ታክስ	*10,780.8*	7,648.4	6,652.3	996.1	15.0	70.9
ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች	**7,536.9**	**8,026.9**	**7,935.3**	**91.6**	**1.2**	**106.5**
ቀጥታ የበጀት ድጋፍና ዕዳ ቅነሳ	**9,842.5**	**8,267.4**	**5,877.4**	**2,390.0**	**40.7**	**84.0**

ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች

ለ2007 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት ወጪ መሸፈኛ ብር 7.5 ቢሊዮን ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች ለመሰብሰብ ዕቅድ ተይዟል፡፡ በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ከዚህ ምንጭ ብር 8.0 ቢሊዮን ገቢ የተሰበሰበ ሲሆን ከዓመቱ ዕቅድ አንጻር የ106.5 በመቶ አፈጻጸም አሳይቷል፡፡

የመሠረታዊ አገልግሎቶች ድጋፍና ዕዳ ቅነሳ

በበጀት ዓመቱ ለወጪ በጀት መሸፈኛ የታቀደው ሌላው የገቢ ምንጭ ከልማት አጋሮች በመሰረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ መልክ የሚገኘው የውጭ ሀብት ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ ስምንት ወራት ከዚህ የገቢ ምንጭ ከታቀዳው ከዕርዳታና ብድር መልክ በድምሩ 9.8 ቢሊዮን ውስጥ ብር 8.3 ቢሊዮን ብር ተገኝቷል፡፡ ይህም ከበጀት ዓመቱ ዕቅድ 84 በመቶ ነዉ፡፡ በቅርቡ ከልማት አጋሮች ጋር በተደረገው የጋራ ግምገማ በፕሮግራሙ መልካም አፈጻጸም የተመዘገበ በመሆኑ ከዚህ የገቢ ዘርፍ የሚገኘው ገቢ በቀጣይ ወራት እንደሚለቀቅ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

3.2.2 የወጪ አፈጻጸም[2]

በ2007 በጀት ዓመት በአገር ውስጥ ገቢ ፣በውጭ ብድርና ዕርዳታ ምንጮች ለመሸፈን የታቀደው ጠቅላላ የፌዴራል መንግስት ወጪ በጀት ብር 163.1 ቢሊዮን ነው፡፡ ከዚህ ወጪ በጀት ውስጥ ለመደበኛ ብር 42.3 ቢሊዮን፣ ለካፒታል ብር 54.8 ቢሊዮን፣ ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የበጀት ድጋፍ 50.9 ቢሊዮን እና ለምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ማጠናከሪያ ድጋፍ ብር 15 ቢሊዮን በጀት ተመድቧል፡፡ የ2007 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት የፌዴራል መንግስት መደበኛ፣ ካፒታልና ለክልሎች ጠቅላላ የበጀት ድጋፍ በድምሩ ብር 110.8 ቢሊዮን ወጪ የተደረገ ሲሆን፣ ከዓመቱ ዕቅድ 68.0 በመቶ አፈጻጸም አሳይቷል፡፡ ከ2006 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከነበረዉ የወጪ አፈጻፀም ደግሞ የዘንድሮው አፈጻፀም በ12.9 በመቶ ብልጫ አለዉ፡፡ በዘጠኝ ወራት ውስጥ ከተደረገው ጠቅላላ ወጪ ውስጥ ለመደበኛ ወጪ የተከፈለው ብር 24.2 ቢ ሊዮን የጠቅላላ ወጪውን 21.9 በመቶ የሚሸፍን ሲሆን፣ ለካፒታል ወጪ የተከፈለው ብር 39.4 ቢሊዮን ደግሞ ከአጠቃላይ ወጪ 35.5 በመቶ ያህል ነው፡፡ በሌላ በኩል ከትሬዠሪ ለክልሎች ድጋፍ (የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች

[2] የዋና ገንዘብ ዕዳ ክፍያን፣ የፕሮጀክቶች ዕርዳታን እና በሚያዝያ ወር የፀደቀውን ተጨማሪ በጀት አያካትትም፡፡

ድጋፍን ጨምሮ) ብር 47.2 ቢሊዮን የተላለፈ ሲሆን፣ ይህም የአጠቃላይ ወጪውን 42.6 በመቶ ድርሻ ይዟል (ሠንጠረዥ 6)፡፡

ባለፉት ዓመታት ተመሳሳይ ጊዜያት ከነበረው የወጪ አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸርም ተመጣጣኝ የነበረና የመንግስት ፊሲካል አፈጻጸም ለኢኮኖሚ ዕድገቱ አስተዋፅኦ በሚያደርግ መልኩ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡

ሠንጠረዥ-6፡ የ2007 በጀት ዓመት ከሐምሌ- መጋቢት ወራት የፌዴራል መንግሥት የመደበኛና የካፒታል ወጪ አፈጻጸም (የክልሎችን የበጀት ድጋፍ ጨምሮ)

/በሚሊዮን ብር/

ዝርዝር	የ2007 የፀደቀ በጀት	መጋቢት ወር		ልዩነት ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወር በመቶኛ	ከሐምሌ-መጋቢት ወራት ክንውን.				የ9 ወር ክንዉን ከፀደቀዉ በጀት
		2007 አፈጻጸም	2006 አፈጻጸም		2007 አፈጻጸም	2006 አፈጻጸም	ልዩነት ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወራት በብር	ልዩነት ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወራት በመቶኛ	በመቶኛ
ጠቅላላ ወጪ	**163,061.3**	**7,511.0**	**12,827.9**	**-41.4**	**110,892.4**	**98,179.2**	**12,713.2**	**12.9**	**68.0**
መደበኛ ወጪ	**42,279.8**	**2,911.4**	**2,639.6**	**10.3**	**24,249.4**	**19,201.2**	**5,048.2**	**26.3**	**57.4**
አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት	14,056.9	1,233.8	1,379.2	**-10.5**	11,387.7	9,801.1	1,586.5	16.2	81.0
የኢኮኖሚ አገልግሎት	2,579.4	154.7	88.0	**75.9**	1,276.0	881.1	394.9	44.8	49.5
ማኅበራዊ አገልግሎት	11,430.7	1,138.3	675.9	**68.4**	8,160.0	5,739.9	2,420.1	42.2	71.4
ልዩ ልዩ ወጪዎች	14,212.8	384.6	496.6	**-22.6**	3,425.8	2,779.1	646.7	23.3	24.1
የካፒታል ወጪ	**54,823.1**	**3,849.6**	**3,625.3**	**6.2**	**39,389.1**	**35,275.2**	**4,113.9**	**11.7**	**71.8**
የኢኮኖሚ ልማት	38,635.8	2,205.1	2,593.0	-15.0	25,074.2	25,125.8	-51.6	-0.2	64.9
የማኅበራዊ ልማት	14,191.2	1,330.7	867.5	53.4	10,842.9	8,461.3	2,381.6	28.1	76.4
ጠቅላላ ልማት	1,996.0	313.8	164.7	90.5	3,472.0	1,688.1	1,783.9	105.7	173.9
ከፒታል ወጪ ወስጥ:				*0.0*					
የአገር ወስጥ ምንጭ	43,089.9	3,581.8	3,227.8	11.0	30,201.3	28,317.5	1,883.8	6.7	*70.1*
የወጭ አገር ብድር	11,733.2	267.8	397.4	-32.6	9,187.8	6,957.6	2,230.1	32.1	*78.3*
የክልሎች ጠቅላላ ድጋፍ	**65,958.4**	**750.0**	**6,563.0**	**-88.6**	**47,253.9**	**43,702.8**	**3,551.1**	**8.1**	**71.6**
የክልሎች ድጋፍ	*50,958.4*	*-*	*4,025.6*	*-100.0*	*39,221.9*	*32,526.0*	*6,695.9*	*20.6*	*77.0*
የክልሎች MDG ማስፈጸሚያ ድጋፍ	*15000*	*750.0*	*2,537.4*	*-70.4*	*8032.0*	*11176.8*	*-3,144.8*	*-28.1*	*53.5*

4. የ2008 በጀት ዓመት ገቢ፣ ወጪና የወጪ አሸፋፈን

4.1 አጠቃላይ ታሳቢዎች

የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ በያዝነው በ2007 በጀት ዓመት ይጠናቀቃል፡፡ የዕትዕ አፈጻጸም ግምገማ እንደሚያሳየው በርካታ ተግባራት በታቀደላቸው መሠረት ተግባራዊ የተደረጉ በመሆናቸው ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት የተመዘገበበት፣ በርካታ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ውጤቶች የተገኙበት እንደሆነ አመልክቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ዕቅዱ በወሳኝነት የተሳካ ዕቅድ መሆኑን አመልክቷል፡፡ ሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ደግሞ ዘላቂና ፈጣን ዕድገቱን በማስቀጠል፣ የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን በማረጋገጥ፣ በኢንዱስትሪ ልማትና የኤክስፖርት መስፋፋት ላይ አተኩሮ በመዘጋጀት ላይ ነው፡፡ የዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫም ዘላቂ የልማት ግቦችን ለማሳካት ተግባራዊ የሚደረጉ አንኳር ጉዳዮችን በተጠናከረ እንቅስቃሴ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ በመንግስት በጀት ተግባራዊ የሚደረጉ ዕቅዶችም በበጀቱ ቅድሚያ በመስጠት ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናሉ፡፡ በመሆኑም ይህ የ2008 በጀት የቀጣዩን አምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማስፈጸም በሚያስችል ሁኔታ የተዘጋጀ ነው፡፡ በጀቱም ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገቱ ቀጣይ እንደሚሆን ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጀ ሲሆን፣ በቀጣዮቹ ዓመታት የገቢ አሰባሰቡ እየተሻሻለ እንደሚሄድ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በዚህ ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀው የ2008 በጀት ዝርዝር የገቢ ታሳቢዎች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

4.1.1 የአጠቃላይ ኢኮኖሚ ታሳቢዎች

- የቀጣዩ አምስት ዓመታት ዕቅድ ፈጣን ፍትሀዊና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገቱን የማስቀጠል እና የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን የማረጋገጥ ዓላማዎች ላይ ያተኮረ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም በ2008 በጀት ዓመትና በቀጣዮቹ አምስት ዓመታት የ11 በመቶ ባለሁለት አሀዝ የአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (Real GDP) አማካይ ዕድገት እንደሚመዘገብ ታሳቢ ተደርጓል፡፡
- የዋጋ ዕድገት ሌላው የአጠቃላይ ኢኮኖሚ ታሳቢ ሲሆን በ2008 በጀት ዓመትና በቀጣዮቹ አምስት ዓመታት የ8 በመቶ አማካይ የዋጋ ዕድገት ታሳቢ ተደርጓል፡፡
- ስለዚህም ከ2008-2012 የአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ ዕድገት በአማካይ 20.4 በመቶ ሲሆን በ2008 በጀት ዓመት የ20.0 በመቶ ዕድገት እንደሚኖረው ታሳቢ ተደርጓል፡፡

- ሌላው የቀጣዩ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ታሳቢ በማኑፋክቸሪንግ ልማት እና በኤክስፖርት መስፋፋት የሚጠበቀው ከፍተኛ አፈፃፀም ነው፡፡ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተዘጋጀው የውጭ ክፍያ ሚዛን ትንበያ መሠረት በ2008 በጀት ዓመት የወጪ ዕቃዎች ገቢ (Value of goods export) የ28.2 በመቶ ዕድገት እንደሚኖረው፣ እንዲሁም የገቢ ዕቃዎች ወጪ (Value of goods import) የ21.6 በመቶ ዕድገት እንደሚመዘገብ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ ከ2008-2012 ባሉት ዓመታት የወጪ ዕቃዎች ገቢና የገቢ ዕቃዎች ወጪ በቅደም ተከተል የ26.6 እና የ16.9 በመቶ አማካይ ዕድገት እንደሚያስመዘግቡ ትንበያው ያሳያል፡፡
- የብር የውጭ ምንዛሬ አፈጻጸምን ስንመለከት በ2006 የአንድ የአሜሪካን ዶላር አማካይ የብር ምንዛሬ ብር 19.1 የነበረ ሲሆን በ2007 በጀት ዓመት ወደ ብር 20.1 ከፍ እንደሚል ተገምቷል፡፡ በ2008 በጀት ዓመት አንድ የአሜሪካን ዶላር የብር አማካይ ዋጋ በ6.2 በመቶ በማደግ ብር 21.3 እንደሚደርስ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ትንበያ ያሳያል፡፡

4.1.2. የፊሲካል ፖሊሲ ታሳቢዎች

- በ2007 በጀት ዓመት የተያዘው የ115 ቢሊዮን የታክስ ገቢ ዕቅድ ሙሉ ለሙሉ እንደሚሰበሰብ ታሳቢ ተደርጓል፡፡
- የ11 በመቶ ኢኮኖሚ ዕድገት ትንበያው ለታክስ ገቢ የሚኖረው አስተዋጽኦ ግምት ውስጥ ገብቷል፡፡
- በተጨማሪም የታክስ አስተዳደሩን ለማሻሻል ታሳቢ የተደረጉ እርምጃዎች ተጠናክረው ለገቢ አሰባሰቡ የተሻለ አቅም እንደሚፈጥር ታሳቢ የተደረገ ሲሆን የታክስ ገቢ ዕድገቱ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ ዕድገት (nominal GDP growth) በመጠኑም ቢሆን የተሻለ እንደሚሆን (positive elasticity) በስሌቱ ውስጥ ገብቷል፤
- የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ገቢ ትንበያ በተለይ የተመሰረተው ታክሱ ከሚጣልበት የገቢ ንግድ ዕቃዎች መጠን (Import tax base)፣ አማካይ የጉምሩክ፣ የኤክሳይዝ፣ የተጨማሪ እሴትና የሱር ታክስ መጣኔዎች (Effective tariff and tax rates) እና ከብር የውጭ ምንዛሬ ጋር የተያያዘ እንዲሆን ተደርጓል፤

- ለታክስ ገቢ ትንበያው በዋናነት የታክስ አስተዳደሩን ለማሻሻል ተግባራዊ የሚደረጉ የለውጥ ሥራዎች የታክስ ገቢ አሰባሰቡን ለማሻሻል የሚያስችሉ እንደሚሆን ከፍተኛ ግምት ተወስዷል፡፡
- ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች ምንጭ በዋናነት በመንግስት መ/ቤቶች ከሚሰጡ አገልግሎቶች ክፍያ፣ ከመንግስት ዕቃዎች ሽያጭ፣ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የመንግስት የዲቪደንድ ድርሻ፣ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከሚገኘው የዘቀጠ ትርፍ እና ሌሎች ገቢዎች ላይ የተመሠረተ ሲሆን በተለይ በ2008 በጀት ዓመት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የመንግስት የዲቪደንድ ድርሻ ገቢ ተሰብሳቢ እንደሚደረግ ግምት ተወስዷል፤
- የውጭ ሀብት ከፕሮጀክቶች ዕርዳታና ብድር እንዲሁም ከፒቢኤስ ዕርዳታና ብድር ምንጮች የሚገኝ ነው፡፡ ከፒቢኤስ የሚገኘው ገቢ ከልማት አጋሮች በተገኘ መረጃ ላይ በመመሥረት ግምቱ የተቀመጠ ሲሆን፣ ከፕሮጀክቶች ዕርዳታና ብድር የሚገኘው ገቢ ትንበያ የተወሰደው ከአስፈጻሚ መ/ቤቶች በተገኘ መረጃ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡
- መንግስት ለበጀት ጉድለት መሸፈኛ የሚወስደው ብድር የተቀመጠውን የገንዘብ ፖሊሲ ዓላማ በሚያሳካ እና የኢኮኖሚ ዕድገቱን በሚደግፍ ሁኔታ እንደሚሆን ታሳቢ ተደርጓል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ታሳቢዎች መሠረት በማድረግ የ2008 በጀት ዓመት ዝርዝር የገቢ በጀት ቀጥሎ ባለው ክፍል ቀርቧል፡፡

4.2 የፌዴራል መንግስት ገቢ

ከላይ የተዘረዘሩ ታሳቢዎችን መሠረት በማድረግ የተሰላው የፌዴራል መንግስት የ2008 ገቢ ዕቅድ በሠንጠረዥ 7 የቀረበ ሲሆን፣ አጠቃላይ የፌዴራል መንግስት ታክስ ገቢ በ2008 በጀት ዓመት ብር 141.2 ቢሊዮን እንደሚሆን ታቅዷል፡፡ ይህም በ2007 እንደሚሰበሰብ ከታቀደው የታክስ ገቢ ጋር ሲነጻጸር የብር 25.7 ቢሊዮን ጭማሪ ወይም የ22.2 በመቶ ዕድገት እንደሚያሳይ ተገምቷል (ሠንጠረዥ 7)፡፡ የታቀደው የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ የሚኖረው ድርሻ በያዝነው በጀት ዓመት ከሚደረስበት 9.1 በመቶ ግምት ወደ 9.3 በመቶ እንደሚያድግ የሚገመት ሲሆን የታክስ ገቢ ግምቱ የታክስ elasticity 1.13 ይሆናል፡፡ ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች በአመዛኙ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የመንግስት ዲቪደንድ ገቢ ድርሻ እና ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ በሚገኘው የዘቀጠ ትርፍ ገቢ ግምት ላይ የተመሰረተ ሲሆን በ2008 በጀት ዓመት ጠቅላላ

ድምሩ ብር 15.9 ቢሊዮን ያህል ገቢ ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች እንደሚገኝ ታቅዷል፡፡ በ2008 በጀት ዓመት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የመንግስት ዲቪደንድ ገቢ እንደሚሰበሰብ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በአጠቃላይ ከዚህ ምንጭ እንደሚሰበሰብ የታቀደው ገቢ በያዝነው በጀት ዓመት ይሰበሰባል ተብሎ ከታቀደው አንጻር መጠነኛ ጭማሪ እንደሚያሳይ ከሠንጠረዥ 7 መረዳት ይቻላል፡፡

ሠንጠረዥ 7: የ2008 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት የገቢ ዕቅድ[3]

(በሚሊዮን ብር)

የገቢ ዓይነት	በ2007 የፀደቀ በጀት	የ2008 የገቢ ዕቅድ	ልዩነት ከ2007 የፀደቀ በጀት	
			በብር	*በመቶኛ*
ጠቅላላ ገቢና የፒቢኤስ ዕርዳታ ድምር	**135,187.9**	**158,135.1**	**22,947.2**	**17.0**
የአገር ውስጥ ገቢ ድምር	**131,053.2**	**157,060.7**	**26,007.5**	**19.8**
የታክስ ገቢ ድምር	**115,516.1**	**141,208.4**	**25,692.3**	**22.2**
ቀጥታ ታክሶች	**29,934.5**	**40,688.4**	**10,753.9**	**35.9**
የአገር ውስጥ ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች	**30,320.2**	**41,212.5**	**10,892.3**	**35.9**
በአገር ውስጥ የሚመረቱ ዕቃች ተጨማሪ እሴት ታክስ	*11,861.2*	*16,122.4*	*4,261.2*	*35.9*
የአገልገሎት ተጨማሪ እሴት ታክስ	*13,592.3*	*18,530.8*	*4,938.5*	*36.3*
በአገር ውስጥ የሚመረቱ ዕቃዎች ኤክሳይዝ ታክስ	*4,300.0*	*5,844.7*	*1,544.7*	*35.9*
ተርን ኦቨር ታከክስ	*71.0*	*40.9*	*-30.1*	*-42.4*
የቴምብር ቀረጥና ሽያጭ	*495.7*	*673.7*	*178.0*	*35.9*
የውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ	**55,261.4**	**59,307.5**	**4,046.1**	**7.3**
የጉምሩክ ቀረጥ /የገቢ ዕቃዎች/	*18,334.4*	*19,676.8*	*1,342.4*	*7.3*
የገቢ ዕቃዎች ኤክሣይዝ ታክስ	*6,172.1*	*6,624.0*	*451.9*	*7.3*
የገቢ ዕቃዎች ተጨማሪ እሴት	*19,974.1*	*21,436.6*	*1,462.5*	*7.3*
ሱር ታክስ	*10,780.8*	*11,570.1*	*789.3*	*7.3*
ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች ድምር	**15,537.1**	**15,852.3**	**315.2**	**2.0**
የፒቢኤስ ዕርዳታ	**4,134.7**	**1,074.4**	**-3,060.3**	**-74.0**

[3] በሚያዝያ ወር የጸደቀውን ተጨማሪ በጀት ጨምሮ

ከውጭ ሊገኝ የሚችለው ሀብት ከልማት አገሮች በሚገኝ መረጃና የፋይናንሱን የፍሰት ታሪክ በማየት የሚገመት ነው። ከዚህ የሚገኘው በPBS በጀት ድጋፍ ሲሆን ይህም በቀጥታ ወደ ፌዴራል መንግሥት ግምጃ ቤት የሚፈስና መንግሥት የበጀት ድልድል የሚያደርግበት ነው። ከዚህ ምንጭ በዕርዳታ መልክ ለ2008 በጀት ዓመት ይገኛል ተብሎ የታቀደው ገቢ ብር 1.1 ቢሊዮን ነው።

በአጠቃላይ በ2008 በጀት ዓመት ከሃገር ውስጥ ገቢ እና ከፒቢኤስ ዕርዳታ ይገኛል ተብሎ የተገመተው የፌዴራል መንግስት ገቢ ብር 158.1 ቢሊዮን ሲሆን በያዝነው በጀት ዓመት ይሰበሰባል ተብሎ ከታቀደው ገቢ ጋር ሲነጻጸር የ17.0 በመቶ ዕድገት እንዳለው መረዳት ይቻላል።

4.3 የመደበኛ ወጪ

የ2007 በጀት ዓመት የወጪ አፈጻጸም አቅጣጫን በመገምገም፣ በቀጣይ የበጀት ዓመት ተጨማሪ በጀት የሚጠይቁ የሶሻልና ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ታሳቢዎችን በመውሰድና እንዲሁም መንግሥት የሚከተለውን የወጪ ፖሊሲ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እና እንዲሁም ሊኖር ከሚችለው የፋይናንስ አቅም አንፃር የ2008 በጀት ዓመትን የመደበኛ ወጪ ለማዘጋጀት ተሞክሯል። የመደበኛ ወጪው ከድህነት ቅነሳ ጋር ለተያያዙ የወጪ ዘርፎች ትኩረት የተሰጠ ሲሆን ለመደበኛ ወጪ ከላይ ከተጠቀሱት መሠረታዊ ታሳቢዎች በተጨማሪ ከፕሮግራም በጀት አሰራር አኳያ ለሚጠበቁ ውጤቶችና ዋና ዋና ተግባራት ማስፈጸሚያ የሚያስፈልጉ ወጪዎች በግምቱ ውስጥ ተካተዋል።

በዚህም መሠረት ለ2008 በጀት ዓመት ብር 50,228.4 ሚሊዮን ብር ለመደበኛ ወጪ ተደገፎ የቀረበ ሲሆን ይህም በ2007 በጀት ለደመወዝ ጭማሪ የፀደቀውን ተጨማሪ በጀት ታሳቢ በማድረግ ከተስተካከለው በጀት የ20.5 በመቶ ዕድገት ያሳያል።

4.4 የካፒታል ወጪ

የፌዴራል መንግሥት የካፒታል በጀት የሚሸፈነው ከአገር ውስጥ ከመንግሥት ግ/ቤት እና ከድርጅት ገቢ እንዲሁም ከውጭ ብድርና ዕርዳታ ነው። የ2008 በጀት ዓመት የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተጠናቆ ሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የሚጀመርበት እንደመሆኑ የተዘጋጀው በጀትም የተጀመሩ የነባር ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ እና በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የታቀዱ ግቦችን ለማስፈፀም አስተዋጽኦ የሚያደርጉ አዳዲስ

የካፒታል ፕሮጀክቶችን በማካተት እና ሊኖር ከሚችለው የፋይናንስ አቅም ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህ ረገድ በተለይ ከመንግሥት ግምጃ ቤት ለፌዴራል መንግሥት የካፒታል ወጪ የሚውለው ለፌዴራል የመደበኛ ወጪ፣ ለብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ከሚላከው የበጀት ድጋፍ እና የዘላቂ ልማት ግቦች ለማስፈጸም እንዲቻል በክልሎች ለሚካሄዱ የካፒታል ወጪ የሚውለው ተቀንሶ የሚቀረው ነው፡፡ በመሆኑም ለ2008 የፌዴራል መንግሥት የካፒታል ወጪ ከመንግሥት ግምጃ ቤት ብር 55,924.7 ሚሊዮን፣ ከድርጅት ገቢ ብር 316.9 ሚሊዮን፣ ከውጭ ዕርዳታ ብር 12,413.6 ሚሊዮን እና ከውጭ ብድር ብር 15,645.5 ሚሊዮን በድምሩ ብር 84,300.7 ሚሊዮን እንደሚሆን ታቅዷል፡፡ ይህም ከ2007 በጀት ጋር ሲነፃፀር የ25.8 በመቶ ዕድገት ያሳያል፡፡

4.5 የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የበጀት ድጋፍ

የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት አብዛኛው ወጪ የሚሸፈነው ከፌዴራል መንግሥት በሚተላለፍ የበጀት ድጋፍ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም መንግሥት በክልሎች ለሚከናወኑት የገጠር መሠረተ ልማት፣ የአቅም ግንባታ እንዲሁም ድህነት ተኮር የወጪ ዘርፎች ትኩረት የሰጠ በመሆኑ ለክልሎች የሚመደበውን የበጀት ድጋፍ በየዓመቱ ጭማሪ እንዲኖረው ተደርጓል፡፡

በዚህ መሠረት ለ2008 በጀት ዓመት ለብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ብር 76,808.7 ሚሊዮን የተደገፈ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ከአገር ውስጥ የፋይናንስ ምንጭ የተመደበው ብር 72,850.1 ሚሊዮን ሲሆን፣ የ2007 በጀት ዓመት ደግሞ ከፌዴራል መንግስት በተጨማሪ በጀት የተላለፈውን ብር 11,322.4 ሚሊዮን የደመወዝ ጭማሪ ጨምሮ የተስተካከለው የበጀት ድጋፍ ከመንግስት ግምጃ ቤት ብር 62,280.7 ሚሊዮን ሆኗል፡፡ በመሆኑም የ2008 በጀት ዓመት የበጀት ድጋፍ ከ2007 በጀት ዓመት ከተስተካለው የበጀት ድጋፍ ጋር ሲነጻጸር ከመንግስት ግምጃ ቤት የብር 10,569.4 ሚሊዮን ወይም የ16.97 በመቶ ዕድገት ያሳያል፡፡ የ2008 በጀት ዓመት ጠቅላላ የክልሎች ድጋፍ ከሁሉም የፋይናንስ ምንጭ በ2007 በጀት ዓመት ከተስተካከለው ድጋፍ ብር 62,842.8 ሚሊዮን ጋር ሲታይ በብር 13,965.9 ወይም በ22.2 በመቶ ዕድገት ያሳያል፡፡

4.6 የዘላቂ የልማት ግቦች (Sustainable Development Goals) ማስፈጸሚያ ድጋፍ

የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች (MDGs) ለማሳካት በክልሎች ለሚካሄዱ የካፒታል ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ በ2007 በጀት ዓመት ብር 15,000.0 ሚሊዮን መመደቡ ይታወቃል፡፡ ከ2008 በጀት ዓመት ጀምሮ ግን የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች በዘላቂ የልማት ግቦች የተተኩ ሲሆን በ2008 በጀት ዓመት በክልሎች ለሚካሄዱ ዘላቂ ልማትና የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን ለማረጋገጥ የሚያግዙ የካፒታል ፕሮጀክቶች ብር 12,000.0 ሚሊዮን ተደግፎ ቀርቧል፡፡

ከዚህ በላይ እንደተመለከተው የመደበኛና የካፒታል ወጪ ጠቅለል ባለ መልኩ የተገለጸ ሲሆን ከዚህ ቀጥሎ የበጀት ዝግጅቱ ታሳቢዎችና ማብራሪያዎች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

5. የ2008 ፕሮግራም በጀት አዘገጃጀትና ድጋፍ

የፌዴራል መንግሥት የ2008 በጀት ዓመት የበጀት ዝግጅት በመንግስት የተቀመጠውን የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ቁልፍ የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን አቅጣጫዎችና ዓላማዎች፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀውን የመካከለኛ ዘመን የማክሮ ኢኮኖሚና የፊስካል ማዕቀፍን መሠረት ያደረገ ሲሆን፣ የዘመኑን በጀት ለማዘጋጀት የተለያዩ ታሳቢዎች ተወስደዋል፣ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ እንዲሁም ከአስፈጻሚ መ/ቤቶች ጋር የውይይት መድረኮች ተዘጋጅተዋል፡፡

በዚህም መሠረት ሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከማስጀመር አንፃር፣ ከመንግሥት የፋይናንስ አቅም፣ መ/ቤቶች ከተሰጣቸው ተልእኮና ማንዴት አኳያ ለውጤቶች፣ ለዋና ዋና ተግባራትና ለፕሮጀክቶች የሚያስፈልገውን ወጪ በመገምገም በጀቱ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ ለፕሮግራም በጀት ዝግጅት እንዲረዳ አመልካች የበጀት ጣሪያ ከዝርዝር መመሪያ ጋር እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ በበጀት ጥሪው መሠረት አስፈጻሚ መ/ቤቶች የበጀት ጥያቄአቸውን አቅርበው ከሥራ ፀባያቸው አኳያ ተከፋፍለው የበጀት ስሚ ተከናውኗል፡፡

5.1 የ2008 የፕሮግራም በጀት ዝግጅት ዋና ዋና ታሳቢዎች

5.1.1 ጠቅላላ ታሳቢዎች

የፕሮግራም በጀት በጀትን ከውጤት ጋር የሚያዛምድ የበጀት አሰራር ስርአት ሲሆን፣ ውጤትን ለመለካት፣ ተጠያቂነትን ለማስፈን፣ ፖሊሲና ስትራቴጂን መሰረት በማድረግ እቅድን ከበጀት ጋር ለማስተሳሰር እና መደበኛና የካፒታል ወጪዎችን ለማቀናጀት የሚያስችል ቁልፍ መሳሪያ ነው፡፡ ለ2008 የፕሮግራም በጀት ዝግጅት ታሳቢ የተደረጉ ዋና ዋና ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የ2008 በጀት ዓመት የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን (GTP) እንዲሁም የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች (MDGs) ዕቅዶች ተጠናቀው በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እና በዘላቂ የልማት ግቦች (Sustainable Development Goals)

የሚተኩ ሲሆን የተዘጋጀው በጀትም ይህንን መሰረታዊ ለውጥ ታሳቢ እንዲያደርግ በማድረግ፣

- በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ለኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን፣ ለኢንዱስትሪ ልማትና ለኤክስፖርት መስፋፋት የተሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት ግምት ውስጥ በማስገባት፣

- በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የከፍተኛ ትምህርትን ከማስፋፋት አንፃር የተያዘውን ግብ ለማሳካት ሊገነቡ የታቀዱ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎችን ታሳቢ በማድረግ፣

- የተጀመረው የሲቪል ሰርቪስ የለውጥ ሰራዊት ግንባታ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ታሳቢ በማድረግ እና የሚገነባው የለውጥ ሰራዊት አስፈፃሚ መ/ቤቶችን ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ እንዲሆኑ እንደሚያስችላቸው ከግምት ውስጥ በማስገባት፣

- የሃብት ድልድሉን ለመምራት በሚያስችል መልኩ መ/ቤቶች አገራዊና የሴክተር እቅዶች ጋር የተሳሰረ የስትራቴጂክ እቅድ ማዕቀፍ ላይ የተመሰረተ በጀት እንዲያዘጋጁ በማድረግ፤

- መ/ቤቶች በተመደበላቸው በጀት የሚያከናውኑት የመሰረተ ልማትና አገልግሎት አቅርቦት ለህብረተሰቡ የሚያስገኙት ውጤቶችና ለውጦች ግምት ውስጥ በማስገባት፣

- የመንግስት መ/ቤቶች የቀረጿቸው ፕሮግራሞች ከየመ/ቤቱ ተልዕኮና ማንዴት ጋር የተጣጣሙ እንደሚሆን ታሳቢ በማድረግ፤

- መ/ቤቶች ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጧቸውን አላማዎች እና ፕሮግራሞች በቅደም ተከተል እንዳቀረቡ ታሳቢ በማድረግ፤

- የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ታቅደው በካፒታል በጀት ሲከናወኑ የነበሩ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ወደ መደበኛ ስራ እንደሚገቡ ታሳቢ በማድረግ የመደበኛ በጀቱ ከፍ እንዲል በማድረግ፣

- የ2008 በጀት ዓመት የሁለተኛው የፕሮግራም በጀት ሳይክል (2007-2009) የሁለተኛ ዓመት እንደመሆኑ በ2007 በጀት ዓመት የታቀዱ ስራዎችን አፈፃፀም መሰረት በማድረግ የየፕሮግራሞቹን ውጤታማነት በመገምገም የ2008 በጀት ዓመት በጀት ከተቀመጠው ስትራቴጂክ ዓላማ፣ ግቦችና ከሚጠበቁ ውጤቶች አኳያ በመገምገም የፕሮግራም በጀት ተዘጋጅቷል፡፡

5.1.2 የመደበኛ ወጪ

- በ2007 መንግስት ለሰራተኞቹ የደመወዝ ጭማሪ ያደረገው በጀቱ ከጸደቀ በኃላ ስለነበር ለበጀት ዓመቱ ለደመወዝ መጠባበቂያ ከተያዘው በጀት ወደ ባለበጀት መ/ቤቶች ዝውውር በማድረግ የደመወዝ ጭማሪው ሲከፈል ቆይቷል፡፡ ሆኖም የ2008 በጀት ሲዘጋጅ ይህንን ጭማሪ በእያንዳንዱ ባለበጀት መ/ቤት በጀት ላይ እንዲታይ በመደረጉ የየመ/ቤቱ የመደበኛ ወጪ ከ2007 ከጸደቀው በጀት ጋር ሲታይ ሊጨምር ችሏል፣

- አዲስ የአስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት እንደሚኖር ታሳቢ የተደረገ ቢሆንም በመ/ቤቶች ዘንድ ከፍተኛ ተጨማሪ ወጪ የሚያስከትል የአደረጃጀት፣ የሰው ኃይልና የደመወዝ ለውጥ እንደማይኖርና ይልቁንም ቁልፍ የማስፈፀሚያ ስልት የሆነውን የሲቪል ሰርቪስ የለውጥ ሰራዊት በመገንባት ተቋማዊ ተልዕኮን በላቀ ደረጃ መፈጸምና ከፍተኛ የወጪ ቁጠባና ወጤታማነት ማረጋገጥ እንደሚሆን ታሳቢ በማድረግ፣

- መ/ቤቶች ከሚጠበቅባቸው ውጤት አኳያ ወጪ ቆጣቢ የሆነ አሰራር፣ የግዥና የንብረት አስተዳደር ስርዓትን በተጠናከረ መልኩ እንደሚተገብሩ ታሳቢ በማድረግ፣

- ከመ/ቤቶች የሚጠበቀው ውጤት እና ከሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት አኳያ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ የግብዓት ወጪዎች በማስላት፣

- የመ/ቤቶቹን የበጀት አጠቃቀም፣ የዋጋ ንረት እንዲሁም በመንግሥት ተመን የወጣላቸውን /ምግብ፣ የውሎ አበል፣ ወዘተ…/ መሠረት በማድረግ፣

- መ/ቤቶች ከሚጠበቅባቸው ውጤት አኳያ አስፈላጊ ለሆኑ ክፍት የስራ መደቦች ተጨማሪ የደመወዝ በጀት በመያዝ፣

- በየመ/ቤቱ የቀረበውን የውጭ ጉዞ ፕሮግራም በመገምገም ለውጭ አገር ውሎ አበልና ትራንስፖርት ወጪ በመመደብ፣
- ቋሚ ዕቃ ግዢን በተመለከተ አዲስ ለተቋቋሙ መ/ቤቶች፣ ቋሚ እቃ ባለመሟላቱ በስራቸው ላይ ተጽእኖ ለሚያሳድርባቸው አስፈጻሚ መ/ቤቶች የተወሰነ በጀት በመደገፍ፣
- ከመንግሥት ግምጃ ቤት ለሚገዙ መሣሪያዎች፣ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የቀረጥ ሂሳብ በእያንዳንዱ መ/ቤት እንዲያዝ በማድረግ፣
- በቅርቡ የተቋቋሙ አዳዲስ መ/ቤቶች ያቀረቡትን የበጀት ጥያቄ ከሚያስመዘግቡት ውጤት አኳያ በመገምገም በተወሰነ ደረጃ በሙሉ አቅማቸው እንደሚሰሩ ታሳቢ በማድረግ ለደመወዝና የስራ ማስኬጃ ወጪ ጭማሪ በማድረግ፣
- በ2007 በጀት ዓመት የተጀመረው የፐብሊክ ሰርቪስ የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ በ2008 በጀት ዓመትም በሰፊው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ታሳቢ በማድረግ፤ በአዲስ አበባ የሚገኙ የፌዴራል መ/ቤቶች ሰራተኞችም ይህንን አገልግሎት እንደሚጠቀሙ ታሳቢ በማድረግ በየመ/ቤቱ የሚያዙ የነዳጅ፣ የተሽከርካሪ ጥገናና ኪራይ ወጪዎች እንደሚቀንስ ታሳቢ በማድረግ፣

5.1.3 የካፒታል ወጪ

- ከመንግሥት የትኩረት አቅጣጫ አንፃር የሁለተኛው የዕድገትና ትራንሰፎርሜሽን ዕቅድ የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን፣ የኢንዱስትሪ ልማትና የኤክስፖርት ማስፋፋት ግቦችን ለማሳካት የሚያስችሉ አዳዲስ የካፒታል ፕሮጀክቶች እንዲሁም በዕቅዱ ዘመን ሊገነቡ ለታቀዱ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች አስፈላጊው በጀት ተደግፏል፡፡
- የ2008 በጀት ዓመት የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አልቆ ሁለተኛው ዕቅድ የሚጀመርበት እንደመሆኑ ባለፉት ዓመታት ተጀምረው ያላለቁ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጋቸው የበጀት ድጋፍ ተደርጓል፡፡

- ❖ በውጭ ፋይናንስ ጭምር ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶች ደግሞ የውጭ ፋይናንስ ፍሰት በእርግጠኝነት በበጀት ዓመቱ ሊፈስ የሚችለውን የገንዘብ መጠን በበጀት እንዲያዝ ተደርጓል፡፡

- ❖ በውጭ ፋይናንስ ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶች ከመንግስት የሚያስፈልገውን ተጓዳኝ ፋይናንስ (Matching Fund) እንዲያዝ ተደርጓል፡፡

- ❖ ከመ/ቤቶቹ ተልዕኮ አኳያ በመደበኛ ተግባር መሰራት ያለባቸው ስራዎችና የመደበኛ ወጪ ይዘት ያላቸው ፕሮጀክቶች እንዲቋረጡ በማድረግ በመደበኛ ወጪ ስራዎቹ እንዲከናወኑ ተደርጓል፡፡

- ❖ የቢሮ ሕንፃ ግንባታን በሚመለከት በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በጀቱ ስለተያዘ በእያንዳንዱ መ/ቤት የቢሮ ሕንፃ ግንባታ በጀት አልተያዘም፡፡ እየጨመረ ከመጣው የመ/ቤቶች የቢሮ ኪራይ ወጪ አንፃር በ2008 በርከት ያሉ የመንግስት ቢሮዎች ግንባታ እንደሚካሄድ ታሳቢ ተደርጎ በጀቱ ተደግፏል፡፡

- ❖ በመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ያለው የፕሮጀክት ስራ አመራር ስርዓት እንዲጠናከር በማድረግ ከትምህርት ጥራትና አግባብነት አኳያ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ፕሮጀክቶች በመለየት እና ለተግባር ትምህርት ለሚያስፈልጉ መሳሪያዎች እና ፋሲሊቲዎች ትኩረት በመስጠት በጀቱ ተደግፏል፡፡

በአጠቃላይ የ2008 በጀት አመት የበጀት ዝግጅት ከፍ ብለው የተመለከቱትን ታሳቢዎችና አቅጣጫዎች ግምት ውስጥ ያስገባና ያስቀመጠ ሲሆን ከመንግሥት የሚመደበው የበጀት ድጋፍም በመደበኛና በካፒታል ወጪዎች በመለየት ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

5.2 ጠቅላላ በጀት

በ2007 በጀት ዓመት ለመደበኛ ወጪ (የተስተካከለ በጀት) ብር 41,732.9 ፣ ለካፒታል ወጪ ብር 66,990.2 ሚሊዮን እንዲሁም ለክልል መንግሥታት ድጋፍ (የተስተካከለ በጀት) ብር 62,842.8 ሚሊዮን እና ለምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ማጠናከሪያ ብር 15,000.0 ሚሊዮን በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ የፀደቀውን ተጨማሪ በጀት ጨምሮ የተስተካከለው በጀት ብር 186,565.9 ሚሊዮን በጀት ተፈቅዶ እንደነበር ይታወሳል፡፡

ለ2008 በጀት ዓመት ለመደበኛ ወጪ ብር 50,288.4 ሚሊዮን፣ ለካፒታል ወጪ ብር 84,300.7 ሚሊዮን እንዲሁም ለክልል መንግሥታት ድጋፍ ብር 76,808.7 ሚሊዮን እና ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ብር 12,000.0 ሚሊዮን ተደግፏል፡፡ በዚህም መሠረት አጠቃላይ የፌዴራል መንግሥት የ2008 በጀት ብር 223,397.8 ሚሊዮን ሲሆን ይህም ከ2007 ከተስተካከለው በጀት በብር 36,831.9 ሚሊዮን ወይም በ19.7 በመቶ ዕድገት ያሳያል፡፡

የ2008 በጀት ድጋፍ

በሚሊዮን ብር

የወጪ ዓይነት	የ2007 የተስተካከለ በጀት	የ2008 የተደገፈ በጀት	ልዩነት	
			በመጠን	በ %
1	2	3	4=3-2	5=4/2
መደበኛ	41,732.9	50,288.4	8,555.5	20.50
ካፒታል	66,990.2	84,300.7	17,310.5	25.84
ክልል ድጋፍ	62,842.8	76,808.7	13,965.9	22.22
የዘላቂ የልማት ግቦች ማጠናከሪያ(SDGs)	15,000.0	12,000.0	(3,000.0)	(20.00)
ድምር	186,565.9	223,397.8	36,831.9	19.74

ከሠንጠረዡ ላይ መረዳት እንደሚቻለው ለ2008 ከተደገፈው በጀት ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ ይዞ የሚገኘው የካፒታል በጀቱ ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ ለክልል መንግሥታት የተመደበው የበጀት ድጋፍ ነው፡፡



የበጀት ድጋፉና ድልድሉ በዋና ዋና ወጪዎች ይህን ሲመስል፣ ለመደበኛና ለካፒታል ወጪዎች የተመደበውን በጀት በአገልግሎትና በሴክተር በመለየት ከዚህ በታች በአጭሩ ለማብራራት ተሞክሯል፡፡

5.2.1 የመደበኛ ወጪ

የ2008 የመደበኛ ወጪ ብር 50,288.4 ሚሊዮን ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ለአስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ብር 16,805.9 ሚሊዮን (33.4%)፣ ለኢኮኖሚ አገልግሎት ብር 2,862.8 ሚሊዮን (5.7%)፣ ለማኀበራዊ አገልግሎት ብር 15,921.1 ሚሊዮን (31.7%) እና ለሌሎች ክፍያዎች ብር 14,698.6 ሚሊዮን (29.2%) ነው፡፡ ከሌሎች ክፍያ ውስጥ ደግሞ ለዕዳ ክፍያ ብር 11,903.7 ሚሊዮን (81%) እንዲሁም ለመጠባበቂያ ብር 2,760.0 ሚሊዮን (18.8%) የተመደበ ነው፡፡

በአጠቃላይ የ2008 መደበኛ ወጪ ለ2007 ከተፈቀደው በጀት በብር 8,555.5 ሚሊዮን ወይም 20.5 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡

የ2008 መደበኛ ወጪ

በሚሊዮን ብር

አገልግሎት	የ2007 የተስተካከለ በጀት	የ2008 በጀት		ልዩነት		ድርሻ በመቶኛ
		የተጠየቀ	የተደገፈ	በመጠን	በ %	
1	2	3	4	5=4-2	6=5/2	
አስተዳደርና ጠቅላላ	14,057.00	18,670.90	16,805.90	2,748.90	19.56	33.4
ኢኮኖሚ	2,579.40	3,287.30	2,862.80	283.4	10.99	5.7
ማኀበራዊ	11,430.70	18,397.40	15,921.10	4,490.40	39.28	31.7
ሌሎች	13,665.80	15,348.60	14,698.60	1,032.80	7.56	29.2
የበጀት ድጋፍ	62.1	34.9	34.9	-27.2	-43.8	
ዕዳ ክፍያ	8,192.60	11,903.70	11,903.70	3,711.10	45.3	
መጠባበቂያ	5,011.10	3,410.00	2,760.00	-2,251.10	(44.92)	
ካሣ ክፍያ	200			-		
ለቀረጥ መልሶ ክፍያ	200			-		
ድምር	**41,732.90**	**55,704.20**	**50,288.40**	**8,555.50**	**20.50**	



5.2.1.1 አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት

በ2008 በጀት ዓመት የተደገፈው በጀት ብር 16,805.9 ሚሊዮን ሲሆን፣ ከ2007 በጀት ዓመት ከተፈቀደው በጀት ብር 14,057.0 ሚሊዮን ጋር ሲነፃፀር የብር 2,748.9 ሚሊዮን ወይም 19.56 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል። ይህም ሊሆን የቻለው ለሀገር መከላከያ ሚኒስቴር፣ ለፌዴራል ፖሊስ፣ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ ለውጭ ጉዳይ ሚ/ር፣ ለፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር እና ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ተጨማሪ የበጀት ድጋፍ በመደረጉ ነው።

5.2.1.2 ኢኮኖሚ አገልግሎት

በኢኮኖሚ አገልግሎት በ2008 በጀት ዓመት ለሥራ ማስፈጸሚያ የተደገፈው መደበኛ በጀት 2,862.8 ሚሊዮን ሲሆን ለ2007 በጀት ዓመት ከተፈቀደው በጀት 2,579.4 ሚሊዮን ጋር ሲነፃፀር በብር 283.4 ሚሊዮን ወይም በ10.99 በመቶ ዕድገት አሳይቷል። ከተደገፈው ጭማሪ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ የትራንስፖርት ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ናቸው።

5.2.1.3 ማኅበራዊ አገልግሎት

ለማኅበራዊ አገልግሎት ለ2008 የተደገፈው በጀት ብር 15,921.1 ሚሊዮን ሲሆን፣ ለ2007 በጀት ዓመት ከተፈቀደው በጀት ብር 11,430.7 ሚሊዮን ጋር ሲነፃፀር የብር 4,490.4 ሚሊዮን ወይም የ39.28 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል። ለጭማሪው ዋናው ምክንያት በ2008 በጀት ዓመት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ የተማሪዎች ቁጥር ከፍ በማለቱ፣ በቅድመ ምረቃ አዳዲስ ፕሮግራሞች ስለሚጀመሩ፣ በድህረ ምረቃ ተጨማሪ ተማሪዎች ስለሚመደቡ ተጨማሪ በጀት ተደግፏል።

5.2.1.4 ሌሎች

ለሌሎች አገልግሎቶች ብር 14,698.6 ሚሊዮን የተደገፈ ሲሆን 81 በመቶ ለዕዳ ክፍያ ሲሆን 18.8 በመቶ ደግሞ ለመጠባበቂያ በጀት እንዲሆን የተደገፈ ነው። በመሆኑም ብር 11,903.7

ሚሊዮን ለዕዳ ክፍያ፣ ብር 2,760.0 ሚሊዮን ለመጠባበቂያ እንዲሁም ብር 34.9 ሚሊዮን ለበጀት ድጋፍ የተደገፈ ነው።

5.2.1.5 መደበኛ ወጪ በኢኮኖሚ ጠቀሜታ

የ2008 ጠቅላላ የመደበኛ ወጪ የደመወዝ፣ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች ወጪ ብር 17,749.8 ሚሊዮን ሲሆን በ2007 በጀት ለደመወዝ ጭማሪ የፀደቀውን ተጨማሪ በጀት ታሳቢ በማድረግ ከተስተካከለው በጀት ጋር ሲነፃፀር የ22.4 በመቶ ወይም የብር 3,252.7 ሚሊዮን ዕድገት ያለው ሲሆን፣ በተመሳሳይ መልኩም የ2008 የሥራ ማስኬጃ ወጪ ብር 32,538.6 ሚሊዮን ከ2007 በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር የ19.5 በመቶ ወይም የብር 5,302.8 ሚሊዮን ጭማሪ አሳይቷል።

የ2008 እና የ2007 የመደበኛ ወጪ የደመወዝ፣ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች እና የሥራ ማስኬጃ በጀት ንጽጽር

በሚሊዮን ብር

አገልግሎት	የ2008 በጀት ዓመት			የ2007 በጀት ዓመት የተስተካከለ በጀት			ልዩነት			
							ደመወዝ፣ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች		ሥራ ማሰኬጃ	
	ደመወዝ፣ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች	ሥራ ማስኬጃ	ድምር	ደመወዝ፣ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች	ሥራ ማስኬጃ	ድምር	መጠን	%	መጠን	%
አስተዳደርና ጠቅላላ	8,673.7	8,132.2	16,805.9	6,608.1	7,448.9	14,057.0	2,065.6	31.26	683.3	9.17
ኢኮኖሚ	1,104.1	1,758.7	2,862.8	929.3	1,650.1	2,579.4	174.8	18.81	108.6	6.58
ማኅበራዊ	6,722.0	9,199.1	15,921.1	4,259.7	7,171.0	11,430.7	2,462.3	57.8	2,028.10	28.28
ሌሎች	1,250.0	13,448.6	14,698.6	2,700.0	10,965.8	13,665.8	(1,450.0)	(53.70)	2,482.80	22.64
ድምር	**17,749.8**	**32,538.6**	**50,288.4**	**14,497.1**	**27,235.8**	**41,732.9**	**3,252.7**	**22.44**	**5,302.80**	**19.47**

5.2.2 የካፒታል ወጪ

የ2008 ጠቅላላ የካፒታል ወጪ ብር 84,300.7 ሚሊዮን ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር 56,241.6 ሚሊዮን ከአገር ውስጥ ምንጭ፣ ብር 12,413.6 ሚሊዮን ከውጭ እርዳታ እና ብር 15,645.5 ሚሊዮን ከውጭ ብድር የሚሸፈን ነው። ጠቅላላ ለካፒታል የተያዘው በጀት ካለፈው በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር የብር 17,310.5 ሚሊዮን ወይም 25.8 በመቶ ጭማሪ ያሣያል።

ለ2007 በጀት ዓመት ተፈቅዶ የነበረው የካፒታል በጀት ብር 66,990.2 ሚሊዮን ላይ ብር 17,310.5 ሚሊዮን ጭማሪ በማድረግ ብር 84,300.7 ሚሊዮን ለ2008 በጀት ዓመት ተደግፏል። ከዚህ ጭማሪ ውስጥ ለኢኮኖሚ ዘርፍ ብር 7,002.0 ሚሊዮን ወይም በ15.8 በመቶ፣ ለማህበራዊ ዘርፍ ብር 5,412.6 ሚሊዮን ወይም በ28.2 በመቶ እንዲሁም ለአስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዘርፍ ለሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ብር 1,545.9 ሚሊዮን ወይም በ74.7 በመቶ ጭማሪ በማድረግ ተደልድሏል። በተጨማሪም በድጋፍ መልክ ብር 4,700.0 ሚሊዮን ተደግፏል። ይኸው ድልድል ካለፈው በጀት ዓመት ከተፈቀደው በጀት ጋር በማነፃፀር በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቧል።

የ2008 ካፒታል ወጪ

(በሚሊዮን ብር)

አገልግሎት	የ2007 የጸደቀ በጀት	የ2008 በጀት		ልዩነት	
		የተጠየቀ	የተደገፈ	መጠን	በ%
1	2	3	4	5=4-2	6=5/2
አስተዳደርና ጠቅላላ	2,069.4	4,910.3	3,615.3	1,545.9	74.70
ኢኮኖሚ	44,393.2	64,182.8	51,395.2	7,002.0	15.77
ማኅበራዊ	19,177.6	37,065.7	24,590.2	5,412.6	28.22
ሌሎች	1,350.0	5,294.1	4,700.0	3,350.0	248.15
ድምር	**66,990.2**	**111,452.9**	**84,300.7**	**17,310.5**	**25.84**



ከላይ የተመለከተውን የ2008 የካፒታል በጀት ድጋፍ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት በዋና ዋና የዘርፍ እና ክፍላተ ኢኮኖሚ በመለየት እንደሚከተለው ጠቅለል ባለ መልኩ ቀርቧል።

5.2.2.1 ከካፒታል ወጪ ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው የ2008 በጀት አመት የካፒታል በጀቱ ሲዘጋጅና ድጋፍ ሲሰጥ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘላቂ ልማት የማምጣት፣ የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽንን የማረጋገጥ እና ድህነትን የማስወገድ ዕቅድን መሠረት ያደረገ በመሆኑ በካፒታል በጀቱ ውስጥ ከፍተኛ ትኩረትና የበጀት መጠን ያላቸው የሥራ ዘርፎች የሚከተሉት ናቸው።

- በመሠረተ ልማት በኩል የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ለዋና መንገዶች፣ አገናኝ መንገዶች ግንባታ እና ነባሮቹን ለማጠናከርና ለማሻሻል ከፍተኛ የበጀት ድጋፍ አግኝቷል። በዚህም መሠረት ለዋና መንገዶች ማጠናከርና ማሻሻል ከመንግሥት ግምጃ

ቤትና ከውጭ ፋይናንስ ብር 5,352.5 ሚሊዮን እና ለአገናኝ መንገዶች ግንባታና ማሻሻያ ብር 24,595.1 ሚሊዮን ተደግፎ ቀርቧል፡፡

❖ የከፍተኛ ትምህርትን ለማስፋፋት ለአዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታና ነባሮቹንም ዩኒቨርሲቲዎች ለማጠናከር ከመንግሥት ግምጃ ቤት ብቻ ብር 16,738.2 ሚሊዮን፣ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርት ብር 217.9 ሚሊዮን እና ለአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፖኬጅ ብር 153.4 ሚሊዮን ተደግፎ ቀርቧል፡፡

❖ ከምግብ ዋስትና ጋር ለተገናኘው ለልማታዊ ሴፍቴኔት ፕሮግራም ከመንግስት ግምጃ ቤትና ከውጭ ፋይናንስ ብር 4,839.9 ሚሊዮን ተደግፏል፡፡

❖ ለጤና ሴክተር ብር 5,557.3 ሚሊዮን ከመንግስት ግምጃ ቤትና ከውጭ ፋይናንስ ተደግፎ ቀርቧል፡፡

❖ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን፣ የኢንዱስትሪ ልማትና የኤክስፖርት ማስፋፋት ግቦችን ለማሳካት ለኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ከመንግስት ግምጃ ቤት ብር 3,000.0 ሚሊዮን ተደግፎ ቀርቧል፡፡

❖ ለመስኖ ልማትና ግድብ ሥራዎች፣ ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ ለተፋሰስ ጥናትና ልማት፣ ለከርሠ ምድር ውሃ ጥናትና ልማት እንዲሁም ለኢነርጂ ልማት በድምሩ ብር 6,516.2 ሚሊዮን ከመንግስት ግምጃ ቤትና ከውጭ ፋይናንስ የተደገፈ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ለኢትዮ ናይል መስኖና ድሬኔጅ ፕሮጀክት ብር 936.8 ሚሊዮን፣ ለከሰም ተንዳሆ መስኖ ልማትና ግድብ ስራ ብር 600.0 ሚሊዮን፣ ለርብ ግድብና መስኖ ፕሮጀክት ብር 490.0 ሚሊዮን፣ ለመገጭ ግድብና መስኖ ፕሮጀክት ብር 425.0 ሚሊዮን፣ ለጊዳቦ ግድብና መስኖ ፕሮጀክት ብር 312.0 ሚሊዮን እና ለአርጆ ዴዴሳ ግድብና መስኖ ፕሮጀክት ብር 310.5 ሚሊዮን የተደገፈ ሲሆን፣ በመጠጥ ውሃ አቅርቦት ፕሮግራም ስር ለሚካሄዱ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ደግሞ ብር 1,844.7 ሚሊዮን ተደግፎ ቀርቧል፡፡

❖ የከተሞችን ልማት ከማፋጠንና አቅም ከመገንባት አንፃር ለከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ፕሮጀክት ብር 1,678.5 ከመንግስትና ከውጭ ፋይናንስ ተደግፎ ቀርቧል፡፡

- በገጠሩ አካባቢ የኤሌክትሪክ ስርጭትን ማስፋፋት በአጠቃላይ ለአገሪቱ ዕድገት መፋጠን፣ ለሕብረተሰብ ኑሮ መሻሻልና ልማትን በማምጣት ድህነት ቅነሳ ላይ ክፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያደርግ በመሆኑ ብር 1,000.0 ሚሊዮን ከመንግስት ግምጃ ቤት ለበጀት ዓመቱ ተደግፎ ቀርቧል፡፡

ከዚህ በላይ የተሰጡት ማብራሪያዎች በዋና ዋና ወጪዎች ላይ ያተኮሩ ሲሆን በአስፈጻሚ መ/ቤቶችና በበጀት ዓይነት በመለየት በጥራዝ ሁለት የበጀት ሠነድ ውስጥ በዝርዝር መግለጫ ተሰጥቶበታል፡፡

5.2.3. የ2008 **የፌዴራል ወጪ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው**

ከዚህ በላይ በፌዴራል የመደበኛና የካፒታል ወጪ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸውን ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የመደበኛና የካፒታል ወጪ ተዳምረው ሲታይ የክፍላተ ኢኮኖሚ ድርሻ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ከአጠቃላይ በጀቱ ውስጥ 66.6 በመቶ ድርሻ ያላቸው መንገድ፣ ትምህርት፣ ግብርና፣ ውሃ፣ ጤና እና የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ናቸው፡፡ በመሆኑም በጀቱ በዘላቂ ልማት፣ በኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን እና በድህነት ተኰር ክፍላተ ኢኮኖሚና የመሠረተ ልማት አውታሮችን በማስፋፋት ላይ ያመዘነ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በፌዴራል ደረጃ የግብርና፣ የጤና እና የውሃ ሴክተር በጀት ድርሻ ከሌሎች አነስተኛ ሆኖ ቢታይም በአብዛኛው ስራዎቹ በክልሎች የሚካሄዱ በመሆኑ የእነዚህ ሴክተሮች የበጀት ድርሻ የክልሎችን ሲጨምር በሀገር ደረጃ ከፍተኛ እንደሆነ ይገመታል፡፡ በተጨማሪም የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽንና ዘላቂ ልማት በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ ትርጉም ላላቸው የማኑፋክቸሪንግ፣ ኤክስፖርትና የከተማ ልማት ዘርፎች ከፍ ያለ በጀት መመደቡን ከሠንጠረዥ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የመከላከያና ዕዳ ክፍያ ደግሞ ከአጠቃላይ በጀቱ ውስጥ 15.9% በመቶ ድርሻ አላቸው፡፡

የ2008 በጀት ዓመት በፌዴራል የመደበኛና የካፒታል ወጪ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው

በሚሊዮን ብር

ተራ ቁጥር	ዋና ዋና ወጪዎች	መጠን	%
1	መንገዶች	33,386.10	24.81
2	ትምህርት	32,927.50	24.47
3	ዕዳ ክፍያ	11,903.70	8.84
4	መከላከያ	9,500.00	7.06
5	ግብርና	9,125.60	6.78
6	ውሃ	6,771.50	5.03
7	ጤና	6,375.40	4.74
8	ፍትህና ደህንነት	5,450.10	4.05
9	የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት	3,000.00	2.23
10	የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን[4]	2,726.10	2.02
11	ትራንስፖርትና መገናኛ	1,197.20	0.89
12	ገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን	1,000.00	0.74
13	ሌሎች	11,226.00	8.34
	ድምር	134,589.20	100

[4] ለመንገዶች የተደገፈውን ሳይጨምር

6. የወጪ አሸፋፈን

በ2008 በጀት ዓመት ከፌዴራል መንግሥት ከሀገር ውስጥ የገቢ ምንጮች እንዲሁም ከውጭ ዕርዳታ እና ብድር በድምሩ ብር 195,754.8 ሚሊዮን እንደሚሰበሰብ ተገምቷል፡፡ ከዚሁ ውስጥ ብር 157,060.8 ሚሊዮን ከአገር ውስጥ፣ ብር 6,676.3 ሚሊዮን ከመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ፣ ብር 13,061.5 ሚሊዮን ከፕሮጀክቶች ዕርዳታ እና ብር 18,956.2 ከፕሮጀክቶች ብድር ሊገኝ እንደሚችል ታቅዷል፡፡

በሌላ በኩል ለፌዴራል መንግሥት የመደበኛ ወጪ 50,288.4 ሚሊዮን (22.5%)፣ የካፒታል ወጪ ብር 84,300.7 ሚሊዮን (37.7%)፣ ለክልሎች ድጋፍ ብር 76,808.7 ሚሊዮን (34.4%) እንዲሁም ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ብር 12,000.0 ሚሊዮን (5.4%) በድምሩ ብር 223,397.8 ሚሊዮን ወጪ ታቅዷል፡፡ በዚህም መሠረት በገቢው ብር 195,754.8 ሚሊዮን እና በጠቅላላ ወጪው ብር 223,397.8 ሚሊዮን መካከል የብር 27,643.0 ሚሊዮን ጉድለት ይታያል፡፡

ይህም የበጀት ጉድለት ማለትም ብር 27,643.0 ሚሊዮን ከሀገር ውስጥ ለመሸፈን ታቅዷል፡፡ የሀገር ውስጥ ብድር መጠኑ ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) ያለው ድርሻ 1.8% ብቻ በመሆኑ የማክሮ ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት ተግባራዊ ከሚደረገው የገንዘብ ፖሊሲ ጋር ተጣጥሞ የሚሄድ በመሆኑ በዋጋ ንረት ላይ ተፅዕኖ እንደማያሳድር ይታመናል፡፡ ዝርዝሩ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥና ሥዕላዊ መግለጫ ተመልክቷል፡፡

የ2008 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት የገቢና ወጪ ዕቅድ ማጠቃለያ (በሚሊዮን ብር)

I. ጠቅላላ ገቢ		**195,754.8**
1.1 ታክስ ገቢ	141,208.5	
1.2 ታክስ ያልሆኑ	15,852.3	
1.3 መሰረታዊ አገልግሎት ከለላ	6,676.3	
1.4 ፕሮጀክት ዕርዳታ	13,061.5	
1.5 ፕሮጀክት ብድር	18,956.2	
II. ጠቅላላ ወጪ		**223,397.8**
2.1 መደበኛ ወጪ	50,288.4	
2.2 ካፒታል ወጪ	84,300.7	
2.3 የክልሎች ድጋፍ	76,808.7	
2.4 ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ	12,000.0	
III. ጉድለት (I – II)		**-27,643.0 (1.8% GDP)**



የ2008 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት ገቢ የውጭ ዕርዳታና ብድር (በሚሊዮን ብር)
18,956.2
8.5%
27,643.0
12.4%
13,061.5
5.8%
6,676.3
3.0%
157,060.8
70.3%
መደበኛ ገቢ
መሠረታዊ አገልግሎት ከለላ
የፕሮጀክት ዕርዳታ
የፕሮጀክት ብድር
የአገር ውስጥ ብድር